**በስመ እግዚአብሔር፡ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ።**
**በስማ ለእግዝእትነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥ እምነ፥ ወንግሥትነ፡**
**ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ወላዲተ አምላክ።**
**በኃይለ መስቀሉ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወመድኃኒነ፥ ካህንነ፥ ወንጉሥነ፡**
**ኢየሱስ ክርስቶስ።**

ይድረስ፡- በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ክህነታዊ ባልደረባዬ ለኾንኸው፡ ለተወደድህና ለተከበርህ ኪዳናዊ ወንድሜ ፈቃደ-ሥላሴ።

በቅርቡ ከጻፍህልኝ እ-ጦማሮች ወዲህ፡ በእግዚአብሔር በረከት፡ እየጨመረ ከኼደው፡ ከተናፋቂው ቤተሰብህ ጋር፡ እንደምን አለህ? ቸሩ ፈጣሪያችን፡ ከነእናቱ ይክበር ይመስገን፡ ቤተሰቤና እኔ፡ በያለንበት፡ ደኅና ነን።

ኅዳር ፳ ቀን፥ ፳፻፲ ዓመተ ምሕረት የጻፍህልንን ደብዳቤ በማያያዝ የላክህልን እ-ጦማርህ ደረሰን፤ እግዜር ይስጥልን!

ስመ ጥምቀቷ፡ ፍቅርተ ሥላሴ የኾነው፡ ሕፃን ማክዳ፡ ባለፈው ደብዳቤዬ ውስጥ ስሟ ሳይጠቀስ የቀረው፡ የኹሉንም ሕፃናት ስም ዝርዝር ለመገልበጥ፡ ከመቀመሪያዬ መዝገብ ቤት ያወጣሁት ሰነድ፡ በስሕተት፡ እርሷ ከመወለዷ በፊት የተጻፈው፥ የታላላቆቿን ስሞች ብቻ የያዘው ኖሮ፡ ያን ባለማስተዋል፡ በዚያ ሰነድ በመጠቀሜ እንጂ፡ እርሷ ተዘንግታ አለመኾኑን ልገልጽልህ እወድዳለሁ። ለዚህም ስሕተቴ፡ ኪዳናዊት ሕፃን ማክዳን፡ ኹለት ጉንጮቿን በመሳም፡ የይቅርታ ጥያቄዬን እንድታቀርብልኝ፡ አደራ ጭምር አሳስብሃለሁ።

ስመ ጥምቀቱ፡ ብርሃነ መስቀል የኾነው፡ ሕፃን ኅሩይና እናቲቱ፡ ኪዳናዊት እመቤት ወለተ ጊዮርጊስ፥ የቀሩትም ሕፃናት፥ ኹላችሁም፡ በጤንነትና በመልካም ኹኔታ ላይ እንደምትገኙ፡ በቅርቡ፡ እቤታችሁ መጥተው ያዩዋችሁ፡ እነኪዳናዊት ስብከተ፡ በእ-ጦማር ስላስታወቁን፡ ደስ አለን፤ የሰማዩ አባታችንንና የሰማዩዋ እናታችንንም አመሰገንን።

አንተታንና አንቺታን በሚመለከት ስንጻጻፍበት የቆየውን ፈታኝ ርእሰ ነገር፡ በመጨረሻ፡ በአንተ ድል አድራጊነት፡ ከመልካሙና ከፍሬያማ ፍጻሜው በመብቃቱ፡ መንፈስ ቅዱስን አመሰገንን፤ በቈራጥነትህ የምንተማመንብህን አንተንም፡ መረቅንህ። ይህ ኪዳናዊ ምግባርህ፡ ወደፊትም፡ ሊገጥምህ የሚችለውን፡ ማናቸውንም ዓይነት፥ ቀጥዬ የማነሣውንና ከአንተው የመጣውን፡ በዚህ ደብዳቤህ የገለጽኸውን የመሰለውን ፈተና ጭምር፡ በአሸናፊነት ለማለፍና ለመወጣት የሚያበቃህ እንደሚኾን አስተማምኖናል።

በአጠቃላይ፡ ለዚህ ጉዳይ፡ ይህን ያህል ትኩረት ሰጥተህ፡ በዚህ ሰፊ መልኩ ማቅረብህ፡ ከአንድ እውነተኛ ኪዳናዊ የሚጠበቅ ምግባር በመኾኑ፡ ይህንኑ አድራጎትህን ከማድነቅ ጋር፡ በአርአያነቱ፡ ለኪዳናውያት እኅቶቻችንና ለኪዳናውያን ወንድሞቻችን፡ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ሳልገልጽ አላልፍም።

ከዚህ ቀጥዬ፡ ወደዋናው የደብዳቤህ መልእክት እገባለሁ። ስገባም፡ በርእሰ ነገሩ መግቢያ ላይ፡ *"ማብራሪያ በመጠየቄ፡ ቅር እንደማትሰኝብኝ በመተማመንና አስተሳሰቤም፡ ስሕተት ኾኖ ከተገኘ፡ ማረሚያ እንደምትሰጠኝ፥ እንዲሁም፡ ያልተገለጸልኝ ካለ፡ እንደምታብራራልኝ በማመን ነው፡ ጥያቄዬንና ሓሳቤን፡ የማቀርበው።"* ብለህ የገለጽኸው አስተያየት፡ አንተን ከመሰለ ኪዳናዊ ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ፡ ትክክለኛው መንፈሳዊ አቋም በመኾኑ፡ አስደስቶኛል፤

ያስደሰተኝም፡ መለኮታዊው መምህራችን፡ ራሱ "ብርሃን" ኾኖ፡ ቃሉንና ትምህርቱን፥ አገልግሎቱንና ምሳሌነቱንም፡ በግልጽ ንግግሩና በብርሃን ሥራው እንዳደረገው ኹሉ፡ እኛም፡ እውነተኞቹ፡ "የብርሃን ልጆቹ" መኾናችንን የምናረጋግጠውና የምናስመሰክረው፡ በጨለማውና በሓሜተኛው ዓለም ለሚኖረው፡ የክፉው ወገን፡ በግልጽና በብርሃን መናገር ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ እርስ በርሳችንም፡ እንዲህ፡ በግልጽነት ልንነጋገር የሚገባ ስለመኾኑ፡ አኹን አንተ በጽሑፍህ ስላመለከትህ ነው፡ "አቋምህ አስደስቶኛል!"" ያልሁህ። ስለዚህ፡ እኔም በዚሁ መንፈሳዊ አቋም ኾኜ፡ የበኩሌን ማብራሪያ፡ በግልጽ አቀርብልሃለሁ።

ይህን የበኩሌን ማብራሪያ ሳቀርብልህም፡ "እንግዴህ፡ እግዚአብሔር እና እመ አምላክ እመቤታችን ድንግል ማርያም፡ እስከዛሬ፡ ለጥያቄዎቼ ኾነ፡ ለስሜቶቼ፡ በአንተ ላይ ዐድረው፡ ምላሽ ሲሰጡኝ እንደነበረ፡ አኹንም፡ ሕሊናዬን ስለሞገተውና ስለፈተነው ጥያቄና ቅሬታ፡ በአንተ ላይ ዐድረው፡ ምላሹን እንደሚሰጡኝ አምናለሁ።" ያልኸውን ሃይማኖታዊ ቃልህን ተመርኵዤ ነው።

ወደዋናው ጉዳይ ከመግባቴ በፊት፡ በማብራሪያዬ ሓተታ ውስጥ አግባብነት ኖሮአቸው የሚነሡ አንዳንድ ቃላት፡ ያላቸው ተዛማጅ ትርጉም፡ እንደሚከተለው ተገልጿል፡-

"ንስሓ"፡ ሰዎች፡ ወንዶችም፥ ሴቶችም፡ አውቀውና ኾን ብለው፡ በድፍረትና በማናለብኝነት፥ በዕብሪትና በክፋት፥ በሥውርም ኾነ፡ በግልጽ፡ በእየራሳቸው ኅሊናና በእግዚአብሔር፥ በሰዎችም ፊት ስለፈጸሙት በደልና ጥፋት፥ ግፍና ኃጢአት፡ በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት፡ በእውነት አዝነውና ተጸጽተው፡ ከክፋው ወደደጉ፥ ከሓሰቱ ወደእውነቱ፥ በመጨረሻም፡ በሥጋዊው፥ በነፍሳዊውና በመንፈሳዊው ኹለንተናዊ ሰውነታቸው፡ ክፋት ከሚያስከትለው ከዘለዓለም ሞት ድነው፡ እግዚአብሔራዊ ለኾነው፡ ለመልካሙ የዘለዓለም ሕይወት የሚበቁበት ሥርዓት ነው።

በስሕተትና ባለማወቅ፥ ያለፈቃድ ተገድዶና ተታልሎ፥ ወይም፡ ሳያውቁ፡ በድንገተኛና በገነፈለ ስሜት፡ የሚፈጸመው ጥፋት፡ በደል፥ ወይም፡ ኃጢአት አይደለም። ይህ እውነታ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ቀርቶ፡ ሰዎች እንኳ፡ "ፍትሕ ርትዕ" ብለው በሚያካኺዱት ሥርዓታቸው፡ ሲሠሩበት ይታያል።

"ጽድቅ" ማለት፡ "እውነት"፥ "ጻድቅ"፥ ወይም፡ "ጻድቃን" ማለት ደግሞ፡ "እውነተኛ"፥ ወይም፡ "እውነተኞች" ማለት ነው።

"ኃጢአት" ማለት፡ "ሓሰት" ማለት ነው፤ ይኸውም፡ "ኃጢአት" የሚለው ስም፡ "ኀጥአ" ከሚለው፡ ከግእዝ ቃል የተገኘ ሲኾን፡ ትርጉሙ፡ "አጣ" ማለት ነው። የታጣው ምንድር ነው፡ "የእግዚአብሔር እውነት ናት"። ስለዚህ፡ "ኃጢአት" ማለት፡ "የእግዚአብሔር እውነት የታጣችበት፥ ወይም፡ የሌለችበት" ማለት ነው። "የእግዚአብሔር እውነት የታጣችበት፥ ወይም፡ የሌለችበት" ደግሞ፡ ምንድር ነው? "ሓሰት" ነው። ስለዚህ፡ የኃጢአት፡ ሌላ ስሙ፡ "ሓሰት" ነው። "ጽድቅ" ወይም፡ "እውነት" በሚለው ቃል አንጻር፡ "ሓሰት" በማለት ፈንታ፡ "ኃጢአት" የሚባለው፡ ከዚህ የተነሣ መኾኑን ማስተዋል ነው።

ዲያብሎስ፡ በመሢሕ ኢየሱስ አንደበት፡ **"ወኢይቀውም በጽድቅ፤ እስመ አልቦ ጽድቅ በኀቤሁ። ወሶበሂ ይነብብ ሓሰተ፡ እምዚአሁ ይነብብ፤ እስመ ሓሳዊ ውእቱ፤ ወአቡሃ ለሓሰት።"**

ማለትም፡ **"እውነት፡ በእርሱ ዘንድ ስለሌለ፡ በእውነት አልቆመም። ሓሰትን ሲናገር፡ ከራሱ ይናገራል፤ ሓሰተኛ፥ የሓሰትም አባት ነውና።"** የተባለው፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ በእርሱ ዘንድ የታጣችበት፥ ወይም፡ የሌለች ስለኾነ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ ዲያብሎስ፥ ወይም ሰይጣን፡ **"ኃጢአተኛ፥ የኃጢአትም አባት ነውና።"** ቢባል ያስኬዳል። (ዮሐ. ፰፥ ፵፬።)

ከዚህ በቀር፡ በዚህ ኾነ፥ በሌሎቹ ጽሑፎቼ ውስጥ፡ አንዳንድ ጊዜ፡ "ኪዳናዊትና ኪዳናውያት" የሚለው፡ የእኅቶቻችን መለያ የኾነው ስያሜ፡ የወንድሞቻችን ከኾነው ቀድሞ ተጽፎ ብታገኝ፡ አንተም ኾንህ፡ ሌሎቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ በዚህ ረገድ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ካለን፡ ኢትዮጵያዊ አቋም የተነሣ፥ ማለትም፡ ኹለቱም ጾታዎች፡ በእኩልነት የሚታዩ በመኾናቸው፡ እንደማይደንቃችሁ ተስፋ አለኝ። ይህን ያልሁት፡ እንደሌላው ኹሉ፡ የኖረው ልማድ፡ አጉልም ቢኾን፡ ሲነካ፡ ግር፥ ወይም፡ ቅር ማሰኘቱ ስለማይቀር ነው።

በእኛ ዘንድ ግን፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ይህን የመሰለው ነገር፡ ለኛ ችግር እንደማይኾን እርግጠኛ ነኝ። ስለዚህ፡ አንዳንድ ጊዜ፤ እኔ ስጽፍ፡ የእኅቶቻችንን ስያሜ ላስቀድም እችላለሁ። የዚህ ምክንያቱ፡ ከላይ ያሳሰብሁት ቍም ነገር እንዳለ ኾኖ፡ በተጨማሪ፡ በኪዳናዊው የምስክርነት ቃል አሰጣጣቸውና በልደት ዕድሜያቸው በኩል፡ ቅድሚያ ስላላቸውም መኾኑን፥ እንድታውቁት ይኹን!

እንግዴህ፡ ለአንተም ደብዳቤ፥ ለእኔም ማብራሪያ፡ መነሻ የኾነውን ርእሰ ነገር፡ ከዚሁ፡ ከራስህ ጽሑፍ ያገኘሁትን፡ እዚህ ላይ በመጥቀስ፡ የማብራሪያ ጽሑፌን እጀምራለሁ። ይኸውም፡-

*"ሕሊናዬን የፈተነውና የምገተው ምላሽህን ያዳመጥሁት፡ 'ሥጋዊ ባሕርይ' በሚል፡ በክፍል ኹለት፡ ከ፴፯ተኛው እስከ፵፫ተኛው ደቂቃ፡ የተሰጠው ምላሽ ነው።"* ካልህ በኋላ፡ እርሱም፡ *"ምናልባት፡ ከቻልን፡ ሌላውን ስሜታችንን እንደምንቆጣጠር፡ እስከጋብቻ ድረስ፡ ከግብረ ሥጋ መታቀብ፥ ካልቻልን ግን፡ ከጋብቻ በፊት፡ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢደረግ፡ እንደተሳሳትን መቍጠር የለብንም።"* ብለህ ያቀረብኸው ቃል ነው።

በመቅረፀ ድምፅ አማካይነት የተካኼደውን ያን፡ የጥያቄና መልስ ዝግጅት፡ ከመስማትህ በፊት፡ "የወሊድ መቆጣጠርን" በሚመለከት፡ ቀደም ብዬ፡ ለአንዱ ኪዳናዊ ወንድማችን የሰጠሁትን የማብራሪያ መልስ እንደተመለከትኸው፡ ከጽሑፍህ ተረድቻለሁ፤ ይህ በመኾኑ፡ በቃል የተደረገውን፡ የጥያቄና መልስ ልውውጥ፡ በጽሑፍ ከተላለፈው ጋር አነጻጽሮ ለማደጋገፍ ሳያስችልህ እንዳልቀረ እገምታለሁ። ካልኾነም፡ ወደፊት፡ ምንጊዜም ማድረጉ፡ አግባብነትም፥ ጠቀሜታም እንዳለው፥ አስፈላጊም እንደኾነ ላስገነዝብ እሻለሁ።

በእኔ በኩል፡ ይህ፡ "ተናገርህ!" የተባልሁት ቃል፥ ቀደም ብሎም በጽሑፍ ያስተላለፍሁት ማብራሪያ፡ በሙሉ የሚያመለክቱት፡ ከጋብቻ ጋር የተያያዘውን ሕይወት ብቻ ነው። ይኸውም፡ እየራሳቸውን፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ጋብቻ እያዘጋጁ ያሉ፡ አንድ ወንድና አንዲት ሴት፡ ገና ከመጀመሪያው፡ ለዚያ ጋብቻ፡ የመፈላለጋቸውና የመፈቃቀዳቸው ጽንሰ ሓሳብ የተገኘው ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መኾኑን በማመን፡ አካኼዳቸውን ከእርሱ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ቀጥለው፡ በመጨረሻ፡ የሕይወት ዓላማቸውና ግባቸው፡ የኾነውን ጋብቻን የሚፈጽሙበት ሥርዓት ነው።

በዚህ፡ በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት፡ ያ ጋብቻቸው "ተፈጸመ" የሚባለው፡ ኹለቱ ደናግል፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በውስጣቸውና በመካከላቸው እንዳለ በማመን፡ ለባልና ሚስትነት ተፈቃቅደው ሲስማሙና ቃል ኪዳናቸውን ሲያደርጉ ነው።

ይህም ሥርዓት፡ እውን ኾኖ፡ መከናወኑ የሚረጋገጠው፡ መለኮታዊው መምህራችን፡ "እብለክሙ! ለእመ ኅብሩ፡ ፪ቱ አው ፫ቱ እምኔክሙ በውስተ ምድር፡ በእንተ ኵሉ ግብር ዘኀሠሡ፡ ይትገበር ሎሙ፡ በኀበ አቡየ ዘበሰማያት። እስመ ኀበ ሀለዉ ፪ቱ ወ፫ቱ ጉቡአን በስምየ፡ ህየ ሀለውኩ አነ ማእከሎሙ።"

ማለትም፡ "እላችኋለሁ! ከእናንተ መካከል፡ ኹለቱ፥ ወይም፡ ሦስቱ፡ በምድር ላይ፡ ስለማናቸውም ስለሚፈልጉት ነገር ቢስማሙ፡ ከሰማዩ አባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። እኒህ ኹለቱ፥ ወይም ሦስቱ፡ በስሜ ዐብረው ኾነው በተገኙበት፡ እኔ፡ በመካከላቸው እገኛለሁና።" ብሎ በሰጠን መመሪያ ቃሉ መሠረት በመፈጸሙ ነው።

ልክ በዚያች ቅጽበት፡ የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓተ ጋብቻ፡ በምድርም፥ በሰማይም፡ "ተፈጸመ!" ተብሎ ይታወጃል። በዚያች ቅጽበትና ከዚያ በኋላ፡ ኹለቱ በሚስማሙበት በማናቸውም ጊዜ፡ ሩካቤ ሥጋን መፈጸም ይችላሉ። ያም፡ ጋብቻ፥ ሩካቤ ሥጋውም፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ንጹሕና ቅዱስ ነው። ሌላው፡ ከዚህ ውጪ የሚደረገው ኹሉ፡ የሰዎች ሥርዓት ነው።

አዎን! በወንድነትና በሴትነት ኹለት ጾታዎች ተከፍለን በተፈጠርንበት ሰውነታችን እንድንኖር፡ ከፈጣሪያችን የተሰጠን ሥርዓት፡ ጋብቻ ብቻ ነው። የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንድናደርግበት፡ የተፈቀደልንም ሥርዓት ጋብቻ ነው። ጋብቻ፡ ከእርሱም ጋር፡ የወንድ ዘርና የሴት ወር አበባ፥ ፍትወተ ሥጋና ሩካቤ ሥጋው፥ ፅንሱም፡ ኹሉም፡ እንደሠሪያቸው፡ እንደእግዚአብሔር፡ ንጹሓትና ቅዱሳት ናቸው። ከዚህ ከንጹሑና ከቅዱሱ ጋብቻ ውጪ ለሚደርሰውና ለሚደረገው ጥፋት፥ ወይም፡ ኃጢኣት፡ መፍትሔ ኾኖ፡ ከእግዚአብሔር፡ ለሰው የተሰጠው ጸጋ፡ ንስሓ ነው።

በዚህ እምነትና ሥርዓት ተጋብተው የሚኖሩ ባልና ሚስት፡ ዘመኑ ባመጣቸው አያሌ ግዳጆች ምክንያት፡ ዐብረው ለመኖር የማያስችላቸው ችግር ደርሶ፡ መራራቁ ግድ በሚኾንባቸው ጊዜ፡ ኹሉን ለመኾንና ለማድረግ፡ ሥልጣኑንና ኃይሉን ከፈጣሪያቸው በተፈጥሮ በተቀዳጁበት በመንፈሳዊ አካላቸውና ባሕርያቸው ተጠቅመው፡ ፍትወተ ሥጋቸውን ሊቋቋሙትና ሊያሸንፉት ይገባቸዋል። ምናልባት ይህን ለማድረግ ተስኗቸው፡ አንዳቸው፥ ወይም፡ ኹለቱም፡ ከዚህ ሥርዓት ውጪ፡ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ቢፈጽሙ፡ ይህንኑ ኃጢኣት፡ በቶሎ፡ በንስሓ እንዲሰረይ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል።

በዚህ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ሥርዓታችን መሠረት፡ ኪዳናዊ ፈቃደ ሥላሴና ኪዳናዊት ወለተ ጊዮርጊስ፡ በእውነተኛ ንስሓችሁ፥ ከእርሱም ጋር፡ በኪዳናዊነታችሁ ምክንያት፡ በሃይማኖታዊውና በመንፈሳዊው ዓይናችሁ ሳታዩት ቀርታችሁ ነው እንጂ፡ የሥርዓተ ተክሊል ጋብቻችሁ፡ በምድር ብቻ ሳይኾን፡ በሰማያት፡ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት፡ እንደቅዱሳኑና ቅዱሳቱ ደናግል የተፈጸመ መኾኑን አውቃችሁ፡ ደስ ሊላችሁ ይገባል። ንስሓ፡ ነሳሒውን፥ ወይም፡ ነሳሒቱን፡ እንደገና፡ መልሶ፡ ፍጹም ድንግል የሚያደርግ ነውና።

አለዚያ! "እብለክሙ፡ ከመ ከመዝ ይከውን ትፍሥሕት በሰማያት፥ በቅድመ መላእክተ እግዚአብሔር፡ በበይነ አሐዱ ኃጥእ ዘይኔስሕ፡ ፈድፋደ፡ እምነ ተስዓ ወተስዓቱ ጻድቃን፡ እለ ኢይፈቅዱ ይነስሑ።"

ማለትም፡ "እላችኋለሁ፤ ንስሓ ከማያስፈልጋቸው፡ ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ፡ ንስሓ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ፡ በሰማያት፡ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት፡ የበለጠ ደስታ ይኾናል።" የሚለው፡ የመምህራችን፡ የመሢሕ ኢየሱስ ቃል፡ "ይታበላል" ልንል ነውን? አይደለም፤ ይጸናል እንጂ፡ አይታበልም። (ሉቃ. ፲፭÷ ፩-፴፪።)

በደብዳቤህ ውስጥ የጠቀስሃቸው የእግዚአብሔር ቃላት ኹሉ፡ በእኛ፡ በኪዳናውያኑና በኪዳናውያቱ የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ የተጠበቁ፥ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ፥ በትክክለኛው የትርጓሜ ባሕርያቸውም ተከትለን፡ የምንፈጽማቸው መኾናችንን፡ ከማንም የበለጠ፡ አንተም ታውቀዋለህ።

ከእነዚህ መካከል አንዱን ለመጥቀስ፡ ጌታችንና መምህራችን ኢየሱስ መሢሕ፡ ስለዝሙት፥ ወይም፡ ስለአመንዝራነት በሚናገርበት ጊዜ ኹሉ፡ የሚያመለክተው፡ ጋብቻን በማፍረስ ረገድ ያለውን ጠንቅ እንጂ፡ ከዚያ ውጪ ያለውን አለመኾኑ፡ ከተናገራቸው ቃላት፡ በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

"አታመንዝር" የሚለውን፡ ከዐሥሩ የእግዚአብሔር ቃላት፡ አንዱ የኾነውን፡ ሃይማኖታዊ ምግባር፡ አክብሮ ለመጠበቅና ለመፈጸም፡ በጋብቻ መወሰን ያስፈልጋል፤ ይገባልም፤ ሌላ ማማረጫ የለም።

እዚህ ላይ፡ ከዐሥሩ የእግዚአብሔር ቃላት መካከል፡ አንዱ የኾነው፡ "አታመንዝር!" የሚለው ርእሰ-አንቀጽ፡ ያለጋብቻና ከጋብቻ ውጪ ከሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ጋር አግባብነት ስላለው፡ በዚህ ረገድ፡ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን፡ ምን እንደሚል፡ ጥቂት ማስረዳት አስፈላጊ ይኾናል።

"አመንዝራነት"፡ ወረተኛነት ነው፤ ማለትም፡ በአንድ ጸንቶ አለመርጋት ነው። ለዝሙት ብቻ ሳይኾን፡ ለሌሎች ግብሮች፥ በተለይና በይበልጥ፡ ለአምልኮም ይውላል። አንዱን ፈጣሪ እግዚአብሔርን ማምለክን ትቶ፡ ሌላ፡ ጣዖትን፡ ማለትም፡ ሕያዋን ፍጡራን የኾኑትን መናፍስትንና ሰዎችን፥ በድን የኾነ ቅርፅን ብቻ ሳይኾን፡ ገንዘብን ጨምሮ፡ ሥጋዊ የኾነውን፡ ሀብትን፥ እውቀትንና ሥልጣንን፡ አምላክ አድርጎ፡ ለዚያ መስገድ ወይም መገዛት፡ አመንዝራነት ነው።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ "የእግዚአብሔር ሥርዓት ነው!" ብለው አምነውበት እየፈጸሙ የኖሩትና የሚኖሩት ጋብቻ፡ እንደአዳምና ሔዋን፡ በእግዚአብሔር መንግሥት፡ እስከሞትና ከዚያም በኋላ በሚጸና አንድነት፡ ህልውናን፡ በሕያውነት ለዘለዓለም መቀጠል ነው።

በዚህ አንጻር፡ በተቃራኒነት ያለው አመንዝራነት ግን፡ ይህን፡ እግዚአብሔራዊ ሥርዓት ትቶ፡ የተቀደሰውን ጋብቻ፡ ኹለቱም ባልና ሚስት፥ ወይም አንዳቸው፡ በፈለጉ ጊዜ፡ እያፈረሱትና፡ እየለዋወጡት፥ እነርሱም፡ እየተፋቱና ከሌላው ጋር ሌላ ጋብቻን እየመሠረቱ፡ ባለመጽናትና በወረት መኖር ነው፤ "እሥራኤል ነን!" የሚሉት፡ አይሁድ፡ በሙሴ ጊዜ ሳይቀር እንደሚያደርጉት ማለት ነው።

ይኸው፡ ከእግዚአብሔር ሥርዓት፡ የወጣው፡ የጋብቻ ሕጋቸው፡ የማሰነ (ብልሹ) መኾኑን፡ በግልጽ በማስታወቅ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ነቅፎባቸው፡ አመንዝራነት፡ ጋብቻን ማፍረስ መኾኑን፡ እንዲህ በሚለው፡ መለኮታዊ ቃሉ አረጋግጧል፡- "ሰማዕክሙ፡ ዘተብህለ ለቀደምትክሙ፤ 'ኵሉ ዘይኅድር ብእሲቶ፡ ይጽሐፍ ላቲ፤ መጽሓፈ ኅዳጋቲሃ፤ ወየሃባ፤ ወይድኃራ።' ወአንሰ እብለክሙ፡- 'ኵሉ ዘይድኅር ብእሲቶ፡ ዘእንበለ ትዘሙ በላዕሌሁ፣ ለሊሁ፡ ረሰያ ዘማ፤ ወዘሰ፡ ኅድገተ፡ አውሰበ፣ ዘመወ።'"

ማለትም፡ "ከእናንተ በፊት ለነበሩት፡ (በኦሪት) የተባለውን ሰምታችኋል፤ ሚስቱን የሚፈታ ኹሉ፡ የፍችዋን ሰነድ ይጻፍላት፤ ይስጣትም፤ ይፍታትም።' እኔ ግን፡ እላችኋለሁ፡- በላዩ ካልሴሰነች በቀር፡ ሚስቱን የሚፈታ ኹሉ፡ ራሱ ያመነዘረ ኾኖ፡ እርሷንም፡ አመንዝራ ያደርጋታል፤ የተፈታችውን የሚያገባ እርሱም፡ አመነዘረ።"

ደግሞም፤ "ሰማዕክሙ ዘተብህለ፡ ለቀደምትክሙ፤ 'ኢትዘሙ!' ወአንሰ እብለክሙ፡- 'ኵሉ፡ ዘርእያ ለብእሲት፣ ወፈተዋ፡ ወድአ፡ ዘመወ ባቲ፡ በልቡ።'"

ማለትም፡ "ከእናንተ በፊት ለነበሩት፡ (በኦሪት) የተባለውን ሰምታችኋል፤ 'አታመንዝር!' እኔ ግን እላችኋለሁ፡- 'ወደሴት ያየ ኹሉ፥ የተመኛትም፡ በልቡ፡ ፈጽሞ፡ በእርሷ አመነዘረ።'" ያለው፡ ያ ወንድ፡ በጋብቻ የተወሰነበት፥ ወይም የሚወሰንበት ጋብቻ እያለ፡ ያ የልቡ ምኞት፡ ያን የጋብቻ ሥርዓተ ሕይወት አፍርሶ፡ ፍቺን እንደፈጸመ የሚያስቆጥረው መኾኑን ለማመልከት ነው። ይህንም እውነታ የሚያረጋግጠው ማስረጃ፡ መምህራችን፡ ስለአመንዝራነት የሚናገረው፡ ጋብቻን በማስመልከት ብቻ በመኾኑ ነው።

ይህም ይታወቅ ዘንድ፡ መምህራችን፡ በዚህ ረገድ የተናገረውን ቃል የያዘውንና የእግዚአብሔር ዕፁብ ድንቅ ምሕረት የታየበትን ታሪካዊ ዜና መዋዕል እስኪ፡ እዚህ ላይ እናዘክረው! ይኸውም፡ የአይሁድ የሕግ ሊቃውንትና ፈሪሳውያን ካህናት፡ ሊፈትኑትና ሊያጠምዱት፡ ጋብቻን በማይመለከተው "የዝሙት ኃጢአት የተያዘች ናት!" ብለው፡ ወንዱን ትተው፡ በእርሷ ላይ ብቻ እንዲፈርድባትና እንድትወገር ለማድረግ፡ ወደእርሱ ስላመጧት ሴት የሚናገረው ነው።

መምህራችንም፡ ላመጧት ከሳሾቿ፡ "ዘአልቦ ኃጢአት እምኔክሙ፡ ቀዲሙ፡ ለይገራ በእብን!"

ማለትም፡ "'እርሷ አደረገች!' ያላችሁትን ኃጢአት ያላደረገ ሰው፡ በመካከላችሁ ካለ፡ እርሱ፡ አስቀድሞ፡ በድንጋይ ይውገራት!" አላቸው።

ነገር ግን፡ ኹሉም፡ ወደኋላቸው ተመልሰው ኼደው፡ አንድም የሚፈርድባት ሰው፤ በዚያ ባለመገኘቱ፡ ብቻዋን ቆማ ለቀረችው ሴት፡ "አነሂ አልቦ ዘእኴንነኪ፤ ሑሪ! እትዊ በሰላም! ወእምዝ ዳግመ ኢተአብሲ!"

ማለትም፡ "እኔም አልፈርድብሽም። ኺጂ! በሰላም ወደቤትሽ ግቢ! ከዚህ በኋላ ግን፡ ደግመሽ አታጥፊ!" ነው ያላት እንጂ፡ ከዚህ በቀር፡ ስለአመንዝራነትና ስለ ኃጢአት፥ ስለሌላም ነገር፡ ምንም የተናገረውና ያደረገው ነገር አልነበረም።

ከዚህ ጋር በተያያዘም፡ እግዚአብሔር የሚወድደውንና የሚቀበለውን፡ የእውነትና የመንፈስ አምልኮን ምሥጢር ለገለጸላት፡ ለዚያች፡ ውኃ ልትቀዳ ለመጣች፡ ለአንዲት ሳምራዊት የገጠር ሴት፡ መምህራችን መሢሕ ኢየሱስ፡ "ሑሪኬ፤ ጸውዒ ምተኪ፤ ወንዒ ዝየ!"

ማለትም፡ "እንግዲያስ፡ ኺጂ! ባልሽን ጠርተሽ፤ ወደዚህ ይዘሽው ነዪ!" ባላት ጊዜ፡ የሰጠችው መልስ፡ "አልብየ ምት።"

ማለትም፡ "ባል የለኝም።" የሚል ነበር።

ጌታችንም መልሶ፡ "ሠናየ ትቤሊ፡ 'አልብየ ምት!' ቀዲሙሰ፡ ኃምስቱ ዕደው ነበሩ ምስሌኪ፤ ወይእዜሰ፡ ዘሀሎ ምስሌኪ፡ ኢኮነ ምተኪ፤ ወዘንተሰ፡ አማነ ትቤሊ።"

ማለትም፡ "'ባል የለኝም' በማለትሽ፡ መልካም ተናገርሽ፤ ከዚህ አስቀድሞ፡ አምስት ወንዶች፡ ዐብረውሽ ይኖሩ ነበርና። አኹን፡ ከአንቺ ጋር ያለው፡ ባልሽ አይደለም። በዚህስ፡ እውነት ተናገርሽ።" አላት እንጂ፡ ጋብቻን ስለሚመለከተው፡ ስለአመንዝራነት፥ ወይም ስለኃጢአት፡ ፈጽሞ አላነሣም። (ማቴ. ፭፥ ፴፩-፴፪ እና ፴፱፤ ፲፱፥ ፫-፲፪። ዮሐ. ፬፥ ፲፮-፲፰፤ ፰፥ ፫-፲፩።)

ስለዚህ፡ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የተፈጸመው ጋብቻ፡ ጸንቶ ባለበት ጊዜ፡ በባልና ሚስቱ፡ በአንደኛው፥ ወይም፡ በሌላው፥ ወይም፡ በኹለቱም በኩል፡ ከጋብቻ ውጪ የሚደረግ ሩካቤ ሥጋ ቢኖር፡ ያ፡ ዝሙት ነው። ምክንያት ፈልጎ በመፋታት፡ ራሱን ጋብቻን ማፍረስ ግን፡ "አታመንዝር!" ያለውን፡ ከአሥሩ፡ የእግዚአብሔር ቋሚ ቃላት፡ አንዱ የኾነውን፡ መተላለፍ እንደኾነ፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ የጌታ ቃል፡ በሚበቃ ያስረዳል።

ለልዑል እግዚአብሔር እና ለዚህ ኹሉ በደል ቤዛ የኾነ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ለወለደች፡ ለድንግል ማርያምም ምስጋና ይድረሳቸውና፡ እነዚህ፡ ኹለቱም ዓይነት "ኃጢአቶች"፡ በንስሓ የሚነጹና የሚስተካከሉ ኾነዋል።

እግዚአብሔር፡ ነፍሳችንን፡ ከእግዚአብሔር አብ፥ ሥጋችንን፡ ከእግዚአብሔር ወልድ፥ መንፈሳችንንም፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ከፍሎ ሲፈጥረን፡ ኹለንተናችንን፡ እንደእርሱ ሥላሴነት፡ በአንድነትና በሦስትነት ብቻ ሳይኾን፡ ፍጹም፡ ንጹሕና ቅዱስ አድርጎ ነው፡ አከናውኖና አሳምሮ የሠራን። ስለዚህ፡ ከእነዚህ አካላትና ባሕርያት የተገኙት፡ የወንድ ዘርና የሴት የወር አበባ፥ እኒህ ወንድና ሴትም የሚፈጽሙት ጋብቻ፥ ከዚህ የተነሣ የሚያደርጉትም ሩካቤ ሥጋ፡ ኹሉም፡ ፍጹም ንጹሓትና ቅዱሳት ናቸው እንጂ፡ አንዳቸውም እንኳ፡ ኃጢአት አይደሉም።

ኃጢአት የሚያደርጋቸው፡ ራሱ ሰው ነው፤ ማለትም፡ ወንዱ፡ ለዓቅመ አዳም፥ ሴቷም፡ ለዓቅመ ሔዋን ሲያደርሱ፡ ከመንፈስ አስተሳሰባቸው፥ ከነፍስ አነጋገራቸውና ከሥጋ አድራጎታቸው በሚሠርፁት፡ በፍላጎት መብታቸውና በመምረጥ ነጻነታቸው፥ በመወሰን ሥልጣናቸውና በመጨረሻ፡ በማድረግ ኃይላቸው ተጠቅመው፡ ከእግዚአብሔር ቅንነት፥ እውነትና መልካምነት ውጪ ሲኾኑ፡ ቅንነቱ፡ ጥመት፥ እውነቱ፡ ሓሰት፥ መልካሙም ክፉ ይኾንና፡ ኃጢአተኛ ከመኾን ያደርሳቸዋል። ይኹን እንጂ፡ በዚህ ጊዜ፡ ያ ኃጢአት፡ በንስሓ ሲወገድ፡ ኃጢአትነቱ ይሰረይና፡ ያ ሰውነት፡ ወደቀደመ ንጽሕናውና ቅድስናው ይመለሳል።

ይህ፡ ጥመት፥ ሓሰትና ክፉው ወገን፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ በሴቶቹም፥ በወንዶቹም ዘንድ፡ እንዲህ፡ ሊሰፍንና ሊንሰራፋ የቻለው፡ እንዲያው አይደለም። ሥር የሰደደ ጽኑ ምክንያት አለው። እርሱም፡ ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ባለማቋረጥ የሚነገረው እውነታ ነው። ያን እውነታ፡ አኹንም፡ እንደገና ልንደግመው ግድ ይኾናል።

አዎን! በቀጥታ፡ ከእግዚአብሔር የተገኙትና የኢትዮጵያ ብቻ የኾኑት፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖትና ምግባር፥ ሥርዓትና ሕይወት፡ እንዲወገዱ ተደርገው፡ በእነርሱ ቦታ የቀዳማውያኑ አይሁድ የኾነችው ኦሪትና የኋለኞቹ ግብፃውያን የኾነው፡ ኦርቶዶክስ በመተካታቸው ምክንያት፡ የጋብቻ ክብር ከመዋረዱ ጋር፡ የወንድ ዘርና የሴት፡ የወር አበባ፥ የፍትወተ ሥጋ ስሜቱና ሩካቤ ሥጋውም፡ እየራሳቸው፡ "ኃጢአት" ተብለውና በኃጢአትነት ተፈርጀው፡ በዚህ ምንነታቸው ብቻ፡ እነሆ፡ ለ፫ሺ እና ለ፩ሺ፮፻ ዓመታት እውቅናን እንዲያገኙ ተደረገ።

ከዚህ የተነሣ፡ በተለይ፡ እየራሳቸውን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ለማብቃት፡ ፍላጎቱ ኖርዋቸው፡ ጥረት በሚያደርጉ፡ ያላገቡ ወንዶችና ሴቶች ላይ የሚደርሰው ፈተናና ሥቃይ፡ እጅግ እንደሚከብድ ግልጽ ነው። ስለዚህ ለዚህ እውነታ፡ ተገቢውን ማብራሪያና አስፈላጊውን መፍትሔ በማበርከት፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በዚህ ረገድ ያለባትን ግዳጅ ለመወጣት፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፡ አግባብነት ያላቸውን መልእክቶቿን፡ በተለያዩ የኅዋ መስመሮች አማካይነት፡ ስታስተላልፍ መቆየቷ ይታወቃል። ይህን ተልእኮዋን፡ እነሆ፡ አኹንም ቀጥላለች።

በኪዳናውያንና በኪዳናውያት ዘንድ እንደሚታወቀውና እንደሚታመነው፡ እግዚአብሔር፡ በመልኩ ለፈጠረውና "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ላለው፡ ሰብአዊ ፍጡሩ፡ የእርሱ የኾነውን እውቀትና ነጻነት፣ ሥልጣንና ኃይል ጭምር ሰጥቶታል። የመምህራችን የመሢሕ ኢየሱስ ሓዋርያ፡ ቅዱስ ጳውሎስ፡ "ብየ ሥልጣን ላዕለ ኵሉ ዘኮነ፤ ወአኮ ኵሉ፡ ዘይበቍዐኒ። ወኵሉ ይትከሀለኒ፤ ወአልቦ ዘእሬሲ ይሠለጥ በላዕሌየ፡ መኑሂ።"

ማለትም፡ "በተፈጠረው ኹሉ ላይ ሥልጣን አለኝ፤ ነገር ግን፡ ኹሉም የሚጠቅመኝ አይደለም። ኹሉን ማድረግ ይቻለኛል፤ በእኔ ላይ ግን፡ እንዲሠለጥንብኝ የማደርገው፡ አንዳችም ነገር ስንኳ የለም።" ብሎ እንደጻፈው ማለት ነው። (፩ቆሮ. ፮፥ ፲፪።)

ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ ከዚህ ሰብኣዊ ተፈጥሮአቸውና ጸጋቸው የተነሣ፡ እኒህን ፍጹም እውቀትና ፍጹም ነጻነት፥ ፍጹም ሥልጣንና ፍጹም ኃይል፡ ከሰው ሳይኾን፡ በቀጥታ፡ ከፈጣሪያቸው እንዳገኟቸው በማመን፡ በአግባብና በሥርዓት፡ እንዴት ሊኖሩባቸውና ሊያገለግሉባቸው፥ ሊጠቀሙባቸውም እንደሚገባቸው፡ የ፲፯ሺ፭፻፲፮ ዓመታቱ ልምድ፡ ከብቅዓትነት አድርሷቸዋል። ከሰውኛው የትምህርት እውቀት፥ ከሰውኛው የፍልስፍና ነጻነት፥ ከሰውኛው፡ ሙሱን ሥልጣንና ከሰውኛው ግብዝ ኃይል ይልቅ፡ የእግዚአብሔር የኾኑትን እውቀትና ነጻነት፥ ሥልጣንና ኃይል ይመርጣሉ። አስተማሪያቸውና መሪያቸው፥ ጠባቂያቸውና መጋቢያቸው፡ እግዚአብሔር ነውና።

የእኛ፡ የኪዳናውያንና የኪዳናውያት ተልእኮ፡ በዚህ እውቀታችንና ነጻነታችን፥ በዚህ ሥልጣናችንና ኃይላችን፡ የተፈጥሮ ወገኖቻችን የኾኑ ወንዶችንና ሴቶችን፡ ለዚህ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ማብቃት እንደኾነ፡ በኹላችንም የቅዱሱ ኪዳን ልጆች ዘንድ ይታወቃል።

እንግዴህ፡ በዚያ፡ አንተ በጠቀስኸው የቃለ ምልልሴ ክፍል፡ ለማስረዳት የሞከርሁት አሳብ፡ ይኼን የሚመስል መኾኑን፡ እስከዚህ፡ በመጠኑ ካቀረብሁ፡ የቀረውን፡ በሚቀጥሉት ገጾች በበለጠ አብራራለሁ።

ያለኀፍረትና ያለፍርሃት፥ ያለይሉኝታና ያለመሠቀቅ፡ እየራሳቸውን፡ "ክርስቲያን ነን!" ብለው፡ በድፍረትና በይፋ ካሳውቁት፡ ከኦርቶዶክሳውያኑና ከካቶሊካውያኑ፥ ከፕሮቴስታንቶቹና ከሌሎቹም መሰሎቻቸው ኹሉ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆችን፡ የሚለያቸው እኮ፡ በእግዚአብሔርና በእናቱ፥ በእየራሳቸውና በሰዎችም ዘንድ፡ ለቅዱሱ ኪዳን፡ እውነተኞችና ታማኞች እንጂ፥ አስመሳዮችና ግብዞች አለመኾናቸው ነው።

በዚህ ረገድ፡ እንኳን ሰው፥ ወይም፡ ዲያብሎስ፡ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርም እንኳ አይታዘባቸውም። ለምን? የሚያስቡት፥ የሚናገሩትና የሚያደርጉት፡ እንደእርሱ፡ እንደእግዚአብሔር ስለኾነ ነው። ማለትም፡ በአስተሳሰባቸውን ቅንነት፥ በንግግራቸው እውነተኝነትና በምግባራቸው መልካምነት፡ መንፈስ ቅዱስ በሚያውቀው፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የእርሱ እውነተኞችና ታማኞች ስለኾኑ ነው።

ይህም፡ በእርግጥ እውን የኾነው፡ ገና በፍጥረት መጀመሪያ ላይ መኾኑን፡ **"ወገብሮ እግዚአብሔር፡ ለዕጓለ እመሕያው፡ በአምሳለ እግዚአብሔር፤ ተባዕተ፥ ወአንስተ ገብሮሙ። ... ናሁ አዳም፡ ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ፤ ያእምር ሠናየ፥ ወእኩየ!**

ማለትም፡ "እግዚአብሔርም፡ ሰውን (የሕያዋንን እናት ልጅ=የሔዋንን ልጅ)፡ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድ እና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። ... እነሆ አዳም፡ መልካምንና ክፉን ለማወቅ፡ እንደእኛ ኾነ!" የሚለው መለኮታዊ ቃል ያረጋግጣል።

በዚህ ቃል መሠረት፡ እኒሁ፡ የእግዚአብሔር ልጆች፥ የኢትዮጵያም ልጆች የኾኑት፡ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን፡ እየራሳቸውን፡ ለተፈጠሩበት፡ ለእግዚአብሔር መልክና እንደእርሱ ለኾኑበት ምንነታቸውና ማንነታቸው ስላበቁ ነው። ይህንም ብቅዓታቸውን፡ ንጉሡ እግዚአብሔርና ንግሥቲቱ ኢትዮጵያ፡ በተቀመጡበት የመንበረ ጸባዖት ዙፋናቸው ፊት ቆመው፡ በይፋ በሰጡት፡ የቃል ኪዳን ምስክርነታቸው፡ አረጋግጠው ያጸኑት በመኾኑ ነው።

በፍጻሜ ዘመንም፡ ከዛሬ ፪ሺ ዓመት በፊት፡ ወደዚህ ዓለም በሰውነት የመጣው፡ የሕያው እግዚአብሔርና የድንግል ማርያም ልጅ፡ ሰውን፡ ለዚሁ ምንነትና ማንነት ካበቃ በኋላ፡ ለዚህ ኪዳናዊ ኢትዮጵያዊነት የበቃው ሐዋርያ፡ "ንሕነሰኬ፡ ኀሊናሁ ለክርስቶስ ብነ!"

ማለትም፡ "እኛማ፡ ዛሬ የምናስበው፡ በክርስቶስ መንፈስ ነው።" ያለውን የመንፈስ ቅዱስ መልእክቱን፥ እኛም፡ በዘወትሩ የኪዳን ጸሎታችን፡ "በዘዚአከ አእምሮ ከለልከነ አንተ፤ ዘተውህበ ለሙስና ዘትካት ብእሴ፡ አድኅንከ በመስቀሉ ለዋሕድ ወልድከ፤ ወሓደስኮ በዘኢይማስን!"

ማለትም፡ "የአንተን እውቀት አቀዳጀኸን። ለጥፋት የተሰጠ፡ የቀደመውን ሰው፡ በአንድያ ልጅህ መሰቀል አዳንህ፤ ባሕርዩ በማይለወጠው፡ በመንፈስ ቅዱስ አደስኸው።" እያሉ የሚያሰሙትን መለኮታዊ እውነት፡ ሕይወት አድርገው፡ በቅድስቲቱ ትንሣኤና በዘለዓለማዊቷ ሰንበት፡ እየኖሩ ስለሚገኙ ነው። (ዘፍ. ፩፥ ፳፯፤ ፫፥ ፳፪። ፩ቆሮ. ፪፥ ፲፮።)

ኪዳናዊ ወንድሜ ሆይ!

የደብዳቤህን ዋና መልእክት በማነብበት ጊዜ፥ ካነበብሁት በኋላም፡ በውስጤ ሠርፆብኝ የነበረውን መንፈሳዊ ስሜት፡ መቼም ፈቅደህልኛልና፥ አንተም፡ ለእኔ፡ በቅንነት አድርገኸዋልና፡ ሳልሸሽግህ፡ በግልጽ የማሳውቅህ፡ በኪዳናዊው ፍቅርና ደስታ ነው። ይኸውም፡ አንተ፡ ያን፡ የጠቀስኸውን የእኔን ቃል ስትሰማ፡ "የእርሱ ነው ወይ?" ብለህ ለማመን እንዳቃተህ ኹሉ፡ እኔም፡ "እንዴ! በውኑ፡ ይህ፡ የማነብበው አሳብ፡ የማነው? የአንድ ኪዳናዊ ወንድሜ አሳብ ነውን?" ብዬ መጠራጠሬ ነው።

ይኹን እንጂ፡ ካነበብሁት በኋላ፡ በመንፈስ የተሰማኝ እውነታ፡ "፩ደኛ፡ የአንተታውን ነገር በሚመለከት፡ ከዚህ በፊት በተለዋወጥናቸው ደብዳቤዎች እንደኾነውና አኹንም ከላይ፡ በደብዳቤዬ መግቢያ እንዳወሳሁት፡ ያን መልእክት፡ አንተ የሰማኸው፡ እኔ በጻፍኩበት መንፈስ ሳይኾን፡ በሥጋዊው እዝነ አእምሮህ ሊኾን ይችላል፤

፪ተኛም፡ በዚያ ቃለ ምልልሴ ውስጥ፡ ቀደም ብዬ፥ እና/ወይም፡ አከታትዬ ከተናገርኋቸው ቃላትና ነገሮች ጋር ባለማያያዝ፡ ለብቻው ለይተህ በመውሰድ አይተኸው ይኾናል!" የሚል ነበር።

በማነብበት ጊዜም፡ ከፊቴ ተደቅኖ፡ ይታየኝ የነበረው፡ "ኢትዮጵያውያን ነን!" የሚሉትን ለይቼ ለመጥቀስ ያህል፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ሰው ከመኾኑ በፊት፥ ሰው ከኾነም በኋላ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን በሚመለከት፡ የሰጠውን መመሪያ ቃል ተከትሎ ባለመፈጸምና ማስጠንቀቂያዎቹንም ሰምቶ ባለመቀበል፤ ከዚያ ይልቅ በኦሪታውያኑ አይሁድ፡ ለሦስት ሺህ ዓመታት፥ በኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች ደግሞ፡ ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት፡ በሃይማኖት ዐዚማቸው የተለከፈውና በምግባር እርሿቸው የተመረዘው፡ የዛሬው ቤተ ክህነት ወገኖች፡ በሰብአዊ ትምህርታቸው የሚያስፋፉትና በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እያደረሱ ያሉት በደል ነበር፡ አዎን! ከፊቴ ተደቅኖ፡ ይታየኝ የነበረው።

ምናልባት፡ የአንተታውን ቀላል ፈተና ተቋቍመህ ለማሸነፍ አቅቶህ የነበረው፡ ከዚህ የተነሣ ስለነበረ መኾኑን፡ አኹን፡ ፈተናውን፡ በድል አድራጊነት ካለፍኸው በኋላ፡ ይህ አገላለጼ፡ በቀላሉ ሊገባህ እንደሚችል እርግጠኛ ነኝ። ይህም፡ መንፈስ ቅዱስ፡ የሚገልጽልንን ኹሉ፡ ያለማመንታትና ያለውልውል፡ ወዲያው በቅጽበት ለመቀበል፡ ኪዳናዊው ምንነታችንና ማንነታችን፡ ምንጊዜም ዝግጁ አድርጎናልና።

አየህ! ኪዳናዊ ወንድሜ! ከእግዚአብሔር አብ ተከፍላ፡ በረቂቁ አካልና ባሕርይ የተፈጠረችው ነፍሳችን፡ በፈጣሪ የሥነ ፍጥረት ጥበብ፡ ይህን የእግዚአብሔር ግዙፍ ፍጡር የኾነውን የሥጋ አካልና ባሕርይ በመልበሷ፡ ከመንፈሳዊው ይልቅ፡ የእርሱ፡ የሥጋዊው ተገዢና ተመሪ በምትኾንበት ጊዜ፡ አስተሳሰቧ፥ አነጋገሯና አድራጎቷ፡ በዓለሙ ሰዎች ዘንድ፥ ይልቁንም፡ "ሃይማኖታውያንና መንፈሳውያን ነን!" በሚሉት ዘንድ ሳይቀር እንደሚታየው፡ ሥጋዊና ምድራዊ እንደሚኾን፡ ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ማብራራት የሚያስፈልገኝ አይደለም።

ከላይ እንደገለጽሁት፡ እኛን፡ ኪዳናውያንንና ኪዳናውያትን የኢትዮጵያ ልጆች፡ ከሌሎቹ የዓለሙ ሰዎች የሚለየን፡ የምናስበው፥ የምንናገረውና የምናደርገው፡ በሥጋዊው አካልና ባሕርይ ሳይኾን፡ በመንፈስ፥ እርሱም፡ በመንፈስ ቅዱሳዊው አካላችንና ባሕርያችን በመኾኑ ነው።

ለዚህ እውነታ ማስረጃነት፡ ወደሩቅ መኼድ የለብንም፤ የቅርቡን፤ ራስህ አምነህበት፡ "አልተወውም!" ብለህ በአጽንዖት የቆየህበትን፡ የ"አንተታውን" ነገር፡ ለምስክርነት መጥቀሱ ይበቃናል፤ ለምን፡ በዚያን ጊዜ፡ እንደዚያ በእንቢተኝነት ጠንክረህ ለመቀጠል ቻልህ? በዚያን ጊዜ፡ አንተ፡ ታስብ፥ ትናገርና ታደርግ የነበረው፡ ነባቢቷ ነፍስህ፡ ትከተል የነበረው፡ ሥጋዊው አእምሮህ የሚላትን ብቻ በመኾኑ እንደነበረ ለመገንዘብ፡ ለማንኛችንም የሚያዳግተን አይደለም። ልማዱ ተይዞ የኖረው፡ በእርሱ ላይ ተቀርጾና ታትሞ በሚገኘው ጽላት ላይና ማኅደር ውስጥ ስለነበረ ነው።

አንተ ግን፡ እውነተኛውና ታማኙ ኪዳናዊ የኢትዮጵያ ልጅ ስለኾንህ፡ "ሃይማኖታውያንና መንፈሳውያን ነን!" የሚሉት እንኳ ሳይቀሩ፡ ኾነው እንደተገኙት፡ እንደብዙዎቹ የሰው ልጆች፡ በፈተናው ሳትሸነፍ፡ በገድልህ ጸንተህ ስለቀጠልህ፡ እግዚአብሔር፡ እንደግዙፉ ሥጋ ኹሉ፡ በዚያው የሥነ ፍጥረት ጥበቡና ቸርነቱ፡ ለነፍስህ ባጎናጸፋት መንፈሳዊ አካሏና ባሕርይዋ መጠቀምን፡ በቈራጥነት መረጥህ።

በዚህ ጊዜ፡ ያ፡ እግዚአብሔርን የሚያስመስልህ መንፈሳዊ አእምሮህ ተከፈተ፤ የእግዚአብሔርንም እውነት፡ እንደፀሓይ ብርሃን አየህ። ይህችን እውነት ተቀብለሃትና አምነህባት፡ በብርሃኗ ልትኼድ በቍርጥ ወስነህ፡ መራመድ ስትጀምር፡ እንዳጻጻፍህ፡ እጅግ ደስ ብሎህ፡ ነጻ መውጣትህ ተሰማህ።

በዚህ ምግባርህም፡ መለኮታዊው መምህራችን፡ "**አንትሙሂ፡ ለእመ ነበርክሙ በቃልየ፡ አማን አርዳእየ አንትሙ። ወተአምርዋ ለጽድቅ፤ ወጽድቅኒ፡ ታግዕዘክሙ።**"

**ማለትም፡ "እናንተ፡ በቃሌ የምትኖሩ ብትኾኑ፡ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ። እውነትንም ታውቋታላችሁ፤ እውነትም፡ ነጻ ታወጣችኋለች።"** የሚለው ቃሉ ተፈጸመ። (ዮሐ. ፰፥ ፴፩-፴፪።)

ከዚህ ድል ለመድረስ፡ የእግዚአብሔር ተቃዋሚው ባላጋራ፡ ካለው ጠንካራ ኃይል የተነሣ፡ የኪዳናዊው ኢትዮጵያዊ እና የኪዳናዊቷ ኢትዮጵያዊት ተጋድሎ፡ እጅግ የረቀቀና የከበደ ኾኖ ይገኛል። ምክንያቱም፡ በዓለሙ ሰዎች ዘንድ፡ ሥጋዊው አእምሮ፡ ከመንፈሳዊው ይልቅ፡ የቱን ያህል በሰፊነ ኹኔታ፡ ተደማጭነትንና ተቀባይነትን ያገኘ በመኾኑ ነው። ይህንም እውነታ፡ ለመረዳትና ለማስረዳት፡ እጅግ ቀላል ነው። ይኸውም፡ ሰብአዊው ፍጡር፡ በክፋት ዝንባሌው፡ በአንድ በኩል፡ፈጣሪ፡ በእግዚአብሔራዊ መልኩ የፈጠረውን፥ በእውቀቱም፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ላሰኘው የመጨረሻ ልዕልና ያበቃውን ማንነቱን የሚያሳውቀውንና ምንነቱን የሚያረጋግጥለትን፡ መንፈሳዊ አእምሮውን፡ በንቀት መተዉና በዕብሪት አሽቀንጥሮ መጣሉ ነው።

በሌላው በኩል ደግሞ፡ ይህንኑ፡ እኩይ መሠሪነቱን በማጠናከር፡ የእግዚአብሔርን እውነት በመከልከልና ለሰይጣናዊውን ሓሰት ግን፡ ሙሉ መብትንና ፍጹም ሥልጣንን በማስጨበጥ፡ "ከዝንጀሮ የተገኘሁ ነኝ!" እንዲል ያደረገውን፡ የሥጋዊ አእምሮውን፡ ወራዳ አስተሳሰብ፡ ዓለሙ በሙሉ፡ በይፋ ተቀብሎ እንዲያምንበት፥ ለልጆቹም፡ እንዲህ በይፋና በሕግ አስገዳጅነት እያስተማረ፡ የበላይ ገዢነቱን፡ በበለጠ እያጸናና እያገነነው እንዲኼድ በመምረጡና በማወጁ፡ በራሱ ግልጽ ሥራ፡ የማስመስከሩ እውነታ ነው።

ታዲያ! የዛሬ ፪ሺ፯ ዓመታት፡ በመለኮታዊ የትስብእት ሥጋው፡ በመስቀል ላይ መተልተልና በደሙ መጐረፍ፡ በሞቱ ጽዋና በመቃብሩም ርደት፡ ፈጽሞ የተደመሰሰውና የተወገደው፡ ይህ፡ አንተ አኹን፡ በሰፊው በዘረዘርኸው አቋም ውስጥ ተሸፍኖና ተሸሽጎ ስለሚገኘው ጠንቀኛ ችግር፡ ምን ልናደርግ ይገባናል?

ይህ ጠንቀኛ ችግር፡ ከሥሩ ተመንግሎ እንዲጠፋ ለማድረግ፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፡ አስፈላጊውን የተልእኮ ገድል በማካኼድ፡ እስከመጨረሻው መታገል፡ አማራጭ የሌለው ግዳጃችን ሊኾን ይገባል።

ለለዚያ፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተዋረሰና እየተላለፈ፡ ከዚህ የደረሰው፡ ይኸው ጠንቀኛ ደዌ፡ በከሃዲውና በዓመፀኛው፥ በአመንዝራውና በደንዳናው ትውልድ ዘንድ፡ እንዲህ እየቀጠለና እየተጠናከረ፥ እየተስፋፋም ሲኼድ፡ በዓይናችን እያየን፡ እኛ፡ የዛሬዎቹ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን፡ እንዴት፡ "እሺ!" ብለን፥ ወይም፡ "ዛሬም እንዳለ ይኹን! ይቀጥል!" ብለን፥ በዝምታ እናሳልፈውን!? ፈጽሞ ልናሳልፈው አይገባም።

"እናሳልፈው!" የሚል አሳብ ቢኖር፡ ያ አሳብ፡ ከዚያው፡ ከሥጋዊው አእምሮ የሚሠርጽ በመኾኑ፡ የእርሱ ደብዛው፥ ወይም ቅሬታው፡ ፈጽሞ ይጠፋ ዘንድ፡ እንዳለፈው የገድልህ ፍሬያማ ውጤት ኹሉ፡ በዚህም ረገድ፡ መንፈሳዊዉን አእምሮህን፡ በተለመደው ቆራጥነትህ በመክፈት፡ በኪዳናዊነትህ እንድትከታተላቸውና እንድታስተውላቸው፡ ከዚህ በታች፡ ያሠፈርኋቸውን፡ የመንፈስ ቅዱስ ማብራሪያዎች፡ አቅርቤልሃለሁ።

አንደኛ፡- በዚህ ርእስ ነገር፡ በእኔ አማካይነት፥ በቃል ድምፅና በጽሑፍ ምንባብ የተላለፈው፡ የመንፈስ ቅዱስ መልእክት፡ መሠረታዊና መነሻ ዓላማው፥ መንደርደሪያውና ብቸኛ ግቡም፡ አንድ ነው፤ እርሱም፡ እግዚአብሔር፡ በመለኮታዊ እጁና ባሕርያዊ ጥበቡ፡ በጥንተ ተፈጥሮ፡ በንጽሓ ጠባይና በቅድስና ባሕርይ፡ አሳምሮና አከናውኖ፡ የሠራው፡ በወንዱና በሴቲቱ፡ የተባዕነትና የእንስትነት ሕዋሳተ ሥጋ ውስጥ ያሠረፀው ዘርና የወር አበባ፡ መልካሙ ጽድቅ (እውነት) እንጂ፡ ክፉው ኃጢአት (ሐሰት) አይደለም።

ሰዎች፡ ወንዶችም፥ ሴቶችም፡ በእየራሳቸው አስተሳሰብና አምልኮ፥ አነጋገርና አድራጎት፡ ተፈጥሮአዊ ከኾነው፡ ከመለኮታዊው ሥርዓት ውጪ ካላሳደፉትና ካላማሰኑት፥ ካላረከሱትና ካላስነወሩት በቀር፡ መልካሙ ጽድቅ ነው። የወንድ ዘርንና የሴት ወር አበባን፡ በጥንተ ተፈጥሮአቸው፡ "ኃጢአት ናቸው!" የሚል ፍጡር ኹሉ፡ በንጽሕናና በቅድስና የሠራቸውን፡ ቅዱሱን ፈጣሪ፡ ልዑል እግዚአብሔርንና ቅድስት እናቱን ድንግል ማርያምን፡ መስደቡ ነው።

ኋላም፡ ይኸው፡ ሰብአዊ ፍጡሩ፡ ከጥቂቶች በቀር፡ አብዛኛው፡ በራሱ የገዛ ክፋት፡ "ጥንተ አብሶ" በሚባለው ጠንቅ፡ በተለከፈ ጊዜ፡ ያ ንጽሕናውና ቅድስናው ስለማሰነ፤ ከፍጥረት በፊት፡ በልጅነት የተገለጸው እግዚአብሔር፡ ኋላ፡ በፍጻሜ ዘመን፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት ተወልዶ፡ በከፈለው፡ የቤዛነት መሥዋዕትነት፡ ያን፡ የወንዱን ዘርና የሴቷን የወር አበባ የሚያስገኘውን ሰብአዊ ሰውነት፡ ከደረሰበት ሙስናው፡ ፈጽሞ አንጽቶና ነጻ አውጥቶታል።

እንዲህ፤ በንጽሓ ጠባይና በቅድስና ባሕርይ፡ አምሮና ተከናውኖ ይኖርበት ወደነበረው፡ ወደቀደመው ጥንተ ተፈጥሮው የመለሰው መኾኑን የሚመለከተው ነው።

በመጨረሻ፡ በመሢሕ ኢየሱስ የተገለጠው እግዚአብሔር፥ በድንግል ማርያም፡ የተገለጠችው ኢትዮጵያም፡ መለኮታዊውን የቤዛነት ትሩፋት፥ ትስብእታዊውንም የመሥዋዕትነት ዋጋ፡ እንዲህ ባለ ኹኔታ፡ ለእልፍ አእላፋት ዘመናት በመክፈል፡ የሰውን ወገን፡ ተቤዥተውታል፤ ታድገውታል፤ ነጻ አውጥተውም፡ ለልዕልና አብቅተውታል።

ነገር ግን፡ ክፉዎቹ፡ ሰብአውያን ፍጡሮች፡ ከክፋቱ መንፈስ ሠራዊት ጋር ተመሣጥረው፡ በኹሉም አግጣጫ ሲፈጽሙበት የኖሩትን፥ ዛሬም፡ እያካኼዱበት ያሉትን፡ ዘርፈ ብዙ የኾነውን ጥቃታቸውን፡ ለማስወገድ፡ ራሷን፡ በአዋጅ ለዓለሙ ያሳወቀችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በዚህ፡ በወንዱ ዘርና በሴቲቱ የወር አበባ ዝክረ ነገር ላይ በማተኰር፡ በእግዚአብሔር እውነት፡ የዲያብሎስን ሓሰት ማጋለጥንና ማስወገድን፥ በዚያም ቦታ፡ እርሷን፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡ መልሶ ማጽናትን፡ የተልእኮዋ አንዱ ዘርፍ ማድረጓ ነው።

በአጠቃላይ፡ በዚህ ርእሰ ነገር፡ በእኔ አማካይነት የተላለፈው፡ የመንፈስ ቅዱስ ግልጽ መልእክት፡ ዋና ዓላማውና ብቸኛ ግቡ፡ ይኸው፡ የወንዱ ዘርና የሴቲቱ የወር አበባ ምሥጢር፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖት ዘንድ፡ ለ፯ሺ፭፻፯ ዓመታት ዕድሜ፡ የነበረው፥ ያለውና የሚኖረው፡ መለኮታዊ ሞገስ፡ እግዚአብሔር የፈጠረው፡ እጅግ መልካም፡ የሥነ ፍጥረት ዕፁብ ድንቅ ሥራ በመኾኑ፡ ፍጹም ያማረና የተወደደ፥ የከበረና ንጹሕ፥ የተባረከና የተቀደሰ ጸጋ መኾኑን አበክሮ መግለጽ ነው።

በዚህ አንጻር፡ ይኸው፡ የወንዱ ዘርና የሴቲቱ የወር አበባ ምሥጢር፡ "ኃፍረትና ጸያፍ፥ ነውርና ኃጢአት፥ ርኵሰትና መርገም ነው!" በማለት፡ ቀደም ብሎ፡ በኦሪታውያኑ አይሁድ፥ ኋላም፡ ተከታትሎ፡ በኦርቶክሳውያኑ ግብፃውያን አማካይነት፡ ወደኢትዮጵያ ሠርፆ የገባው መሠሪ አስተሳሰብ፡ የእግዚአብሔርን ፍጹም ቅድስናና ደግ ፈጣሪነት የሚቃረን፡ ሓሰትና ሰይጣናዊ መኾኑን፡ አበክሮና አዘክሮ ማብራራትና ማረጋገጥ እንደኾነ፡ ልገልጽ እወድዳለሁ።

ኹለተኛ፡ በዚህ ረገድ ለተነሣው ርእሰ ነገር፡ ማሠሪያውም፥ መፍቻውም፡ ንስሓ የመኾኑ ቍም ነገር አያጠያይቅም። በእኔም ተልእኮ፡ ከሕፃንነቴ ጀምሮ፡ ዓቢይ የኾነውን ክፍል የያዘው፥ እስከዛሬና ዛሬም ያለው፥ ለወደፊቱም፡ የሚቀጥለው፡ ይኸው የንስሓ ፍጹም አስፈላጊነት መኾኑ፡ በአንክሮና በተዘክሮ ሊታወቅ ይገባል።

ሦስተኛ፡ አንድ ኪዳናዊ እና አንዲት ኪዳናዊት፡ ለዚያ ምንነታቸውና ማንነታቸው በሚበቁበት ጊዜ፡ ከላይ እንደተብራራው፡ ኹሉን ነገር የሚሰሙትና የሚያዩት፥ የሚያመዛዝኑትና የሚያስተውሉት፥ የሚናገሩትና የሚያደርጉት፡ በመንፈስ ቅዱስ በተቃኘው፡ በዚያ በመንፈሳዊው ሕዋሳታቸው ብቻ ነው።

ከዚያች ከበቁባት አፍታ አንሥቶ፡ ወንዱ፡ በሚያስበው፥ በሚናገረውና በሚያደርገው ኹሉ፡ ልክ እንደመሢሕ ኢየሱስ ይኾናል፤ ሴቲቱም፡ በምታስበው፥ በምትናገረውና በምታደርገው ኹሉ፡ ልክ እንደድንግል ማርያም ትኾናለች።

ተቀባይነት ያለው እውነታ ይህ ከኾነ፡ አንተ፡ የፈረድክበት ኃጢአተኛ ወንድ፥ ወይም፡ የፈረድክባት ኃጢአተኛ ሴት፡ በኢየሱስ መሢሕ እና በድንግል ማርያም ፊት የሚቀርቡ ቢኾን፡ የእናትና ልጇ ውሳኔ፡ የአንተን መስሎ ይገኛል? ትላለህ? እርሱ ባለቤቱ፡ ኢየሱስ መሢሕ፡ ሲቸግረውና ሲያስፈልገው፡ ይህን የመሰለውን ኹኔታ ለሚያደምጡት ሕዝብ፡ የእርሱን አባትነትና እነርሱም፡ ለልጆቻቸው ያላቸውን ወላጅነት፡ ምሳሌ አድርጎ እያነጻጸረ በማቅረብ፡ ያስተምራቸው እንደነበረው፡ አንተም፥ እኔም፡ በልጆች ተባርከናልና፥ ይኼን እውነታም፡ በቀላሉ፡ በእየራሳችን አስተሳሰብና ድርጊት ልናውቀው ይቻለናልና፡ እስኪ ዳሰስ አድርገነው እንለፍ!

አያድርገው እንጂ፥ ከልጆቻችን መካከል፡ አንዳቸው፥ ወይም፡ ቍጥራቸው፡ ከዚያ ቢበልጥም፡ ምንም አይደለምና፡ የቱንም ያህል ቢበድሉን፥ የቱንም ያህል ቢያስቀይሙን፡ ተቀይመን፥ እኛው ራሳችን፡ ልንበቀላቸው፥ ወይም፡ ልንጎዳቸው ቀርቶ፡ በሌላ በኩል እንኳ ጉዳት እንዲደርስባቸው፥ እንዲጠፉ፥ ወይም፡ እነርሱ በይቅርታ ለመመለስ ባይፈልጉ እንኳ፡ እንደወጡ እንዲቀሩ፡ በውሳጣዊው ሰውነታችን ልናስበውና ልንፈቅደው፡ ከቶ ዓቅሙ ይኖረናልን? የሚኖረን አይመስለኝም።

በዚህ ረገድ፡ ፈጣሪ፡ በአንድ ወገን፡ በመልኩ ፈጥሮና "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኹኑ!" ብሎ፡ በእውን፡ የእርሱ የዘለዓለም ልጆቹ ላደረጋቸው፥ ራሱንም፡ "'አባታችን!' ብትሉኝ!" ላላቸው ሰብአውያን ፍጡሮቹ፡ ያለውን ፍቅር፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ ሰዎች፡ ለልጆቻቸው ያላቸውን ፍቅር በማነጻጸር፡ መለኮታዊው መምህራችን፡ የተናገረውን ስንሰማ፡ ምን እንላለን?

ይኸውም፡ "ወሶበ እንዘ እኩያን አንትሙ፡ ተአምሩ፡ ሠናየ ሀብተ ሠናያተ፡ ውሂበ ለውሉድክሙ፡ እፎ ፈድፋደ፡ አቡክሙ ዘበሰማያት፡ ይሁብ ሠናየ፡ ለእለ ይስእልዎ!?"

ማለትም፡ "እናንተ፡ ክፉዎች ስትኾኑ፡ ለልጆቻችሁ፡ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ፡ በሰማያት ያለው አባታችሁ፡ ለሚለምኑት፡ እንዴት አብልጦ፡ መልካም ነገርን ይሰጣቸው!?" የሚለው ነው። (ማቴ. ፯፥ ፲፩።)

ይህንም ስል፡ "ከእኔ ይልቅ፡ ልጁን የሚወድድ፡ ለእኔ ሊኾን አይገባም!" የሚለውን ዘንግቼው አይደለም፤ ከዚያ ውጭ ያለውንና የሚኾነውን ማለቴ ነው። (ማቴ. ፲፥ ፴፯።)

በኪዳናዊነታችን፡ የምናስበው፥ የምንናገረውና የምናደርገው ኹሉ፡ ሴቶቹ፡ እንደድንግል ማርያም፥ ወንዶቹም፡ እንደኢየሱስ መሢሕ መኾኑን፤ አውቀናል፤ ተረድተናል። ይኹን እንጂ፡ ለዝንተ ዓለም፡ የዚህ ዓለም ሰዎች፥ ይልቁንም፡ በሃይማኖቱና በመንፈሳዊነቱ ዘርፍ በኩል፡ "የእግዚአብሔር፡ ተጠሪዎችና ባለአደራዎች ነን!" የሚሉት፡ የቤተ ክህነቱ ሰዎች ሳይቀሩ፡ እግዚአብሔርና እናቱ፡ በዚያ ማንነታቸው፡ ለፍጡራቸው፥ በይበልጥም፡ ለደካማውና መልካሙን ለማድረግ ለተሣነው፥ ግራ ለገባውና ዓቅም ላነሰው፥ በውስጡ የሚሰማውንና የጨነቀውን ማንም ሊያውቅለት ላልቻለውና ተስፋቢስ ለኾነው ሰብኣዊ ፍጡራቸው፡ **"ምንም ይኹን፡ ምን! ብቻ፡ በኾነው ኹኔታ ይዳንልን! ግድየለም!"** ብለው፡ ወሰን በሌለው፡ በሰፊ ቸርነታቸው፡ ይድንበት ዘንድ፡ የለገሡትን፡ ኍልቈ መሣፍርት ጸጋ፡ ይኸው፡ "ሰው" የተባለው ወገናቸው፡ ጠባብና ውሱን በኾነው፡ በራሱ ሰብኣዊና ሥጋዊ የጭካኔ አስተሳሰቡ፡ ለምን ያጠብበታል? ለምንስ ይወስንበታል? እንዲያውም፡ አልፎ ተርፎ፡ ለምን ይከለክለዋል? ለምንስ ያስቀርበታል?

ስለዚህ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ኹላችን፡ ኪዳናዊነታችን፡ የተፈጥሮ ወገናችን የኾነውን ሰብኣዊ ፍጡር ብቻ ሳይኾን፡ ፍጥረትን በመላ፡ የምናየውና የምንቀበለው፥ የምንተባበረውና የምናገለግለው፡ አባታችን እግዚአብሔር እና እናታችን ኢትዮጵያ፡ እነርሱ፡ ለእኛ እንደኾኑልንና እንዳደረጉልን ኹሉ፡ እኛም፡ ለሌላው የምንኾነውና የምናደርገው፡ በእነርሱ ፍቅርና ርኅራኄ፥ ካልኾነ፡ ታዲያ፡ ኪዳናዊነታችን፡ ምኑ ላይ ነው?

በድንግል ማርያም፡ እናት መሠዊያነትና በልጇ በኢየሱስ፡ መሢሕ ቤዛነት በተገኘው፡ በመንፈስ ቅዱስ የእውነት አምልኮ የተተከሉትን ቃላትና ትእዛዛት፥ ሕግጋትና ሥርዓታት፡ እንደወግ አጥባቂዎቹ ኦሪታውያን በመጠቃቀስ፡ የሰዎች ክፋት ካመጧቸው ከነዚህ ቀንበሮች ኹሉ፥ ቢያንስ ቢያንስ፡ የዛሬ ፪ሺ፯ ዓመታት ነጻ የወጣውን መከረኛ ሰብኣዊ ፍጡር፡ እንደገና፡ ወደነበረበት መከራና ሥቃይ የመለሱትን የዛሬዎቹን፡ መንፈሳውያን የሃይማኖት መሪዎች፡ እኛ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ እንኳንስ ልንከተላቸው፤ ልንመስላቸውስ ይገባናልን? አይገባንም። ጌታችን፤ መምህራችን፡ ስለእነዚህ ጕዶች ያስጠነቀቀንማ፡ **"ዑቁ! ወተዐቀቡ! እምብሑአሙ ለፈሪሳውያን፥ ወሰዱቃውያን!"**

ማለትም፡ **"ተጠንቀቁ! ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠበቁ!"** ብሎ ነው። (ማቴ. ፲፮፥ ፮።)

እርሱም፡ ስለጠንቀኝነታቸው፡ የእነርሱን ነገር፡ በዚህ ማስጠንቀቂያው ብቻ አላቆመውም። ከብዙዎቹ ሌሎች ማስጠንቀቂያዎቹ መካከል፡ እዚህ ላይ፡ ከያዝነው ርእሰ ጉዳይ ጋር፡ አግባብነት ያላቸውን፡ ጥቂቶቹን፡ እስኪ ልጥቀሳቸው!

"ወየአስሩ ፆረ ዓቢየ ወክቡደ፤ ወያሰክምዎ ለሰብእ፡ ዲበ መትከፍቱ፤ ወለሊሆሙሰ፡ ኢይለክፍዎ በአጽባዕቶሙ ጥቀ፡ ለውእቱ ፆር። ...አሌ ለክሙ፡ ጸሓፍት ወፈሪሳውያን መደልዋን! እስመ ተዐጽዉ መንግሥተ ሰማያት፡ ቅድመ ገጹ ለሰብእ፤ አንትሙሂ ኢትበውኡ፤ ወለእለሂ ይበውኡ፡ ትከልእዎሙ በዊአ።"

ማለትም፡ "ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው፡ በሰው ትከሻ ይጭናሉ፤ እነርሱ ግን፡ በጣታቸው ስንኳ፡ ሊነኩት አይወድዱም። ...እናንተ ግብዞች! ጻፎችና ፈሪሳውያን! የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ በሰው ፊት ስለምትዘጉ፡ ወዮላችሁ! እናንተ አትገቡም፤ የሚገቡትንም፡ እንዳይገቡ፡ ትከለክላላችሁ።"

ባለምሥራቹ፡ ቅዱስ ማቴዎስ፡ እንዲህ፡ "መንግሥተ ሰማያት" ያለውን፡ ሌላው ባለምሥራች፡ ቅዱስ ሉቃስ ደግሞ፡ "አሌ ለክሙ፡ ጸሓፍተ ሀገር ወፈሪሳውያን! እስመ ትነሥኡ መራኁተ ጽድቅ ወአእምሮ ወተኀብኡ። ለሊክሙኒ ኢትበውኡ፤ ወለእለሂ ይበውኡ፡ ትከልእዎሙ በዊአ።"

ማለትም፡ "እናንተ፡ የሕግ አዋቂዎችና ፈሪሳውያን! የእውነትንና የእውቀትን ቍልፎች ይዛችኋልና፥ ደብቃችኋልምና።" ብሎ፡ "የእውነትንና የእውቀትን ቍልፎች" በማስመሰል ተርጉሞታል። ቅዱስ ሉቃስ፡ "መንግሥተ እግዚአብሔር" የሚላት መንግሥተ ሰማያት፡ በእግዚአብሔር እውነትና እውቀት ብቻ የምትገኝ፥ በእነርሱም የሚገቡባት ስለኾነች፡ የኹለቱም ባለምሥራቾች አገላለጽና አሰያየም ያስኬዳል። (ማቴ. ፳፫፥ ፬ እና ፲፫-፲፬። ሉቃ. ፲፩፥ ፶፪።)

ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ የእግዚአብሔርን ቃላት መጠቃቀስ ካስፈለገን፡ እስኪ፡ ከምንነጋገርበት ቍም ነገር ጋር፡ ነክነት ያላቸውን፡ ጥቂቶቹን፡ እዚህ ላይ እናንሣቸው!

መምህራችን፡ መሢሕ ኢየሱስ፡ ለደቀ መዛሙርቱ፡ «ወእመኒ አበሰ ለከ፡ እኁከ፣ ሖር! ወገሥፆ በባሕቲትከ በባሕቲቱ፡ አንተ፥ ወውእቱ፤ ...ወእመሰ ኢሰምዐከ፡ ንሣእ ምስሌከ በዳግም፡ አሐደ፥ አው ክልኤ።"

ማለትም፡ "ወንድምህ፡ ቢበድልህ፡ (እዚህ ላይ፡ ማስተዋል ይገባል፡ "ብትበድለው!" አላለም፤ ያለው፡ "ቢበድልህ!" ነው) ብቻህን ኾነህ፥ ...ካልሰማህም፡ ፩ ወይም፡ ፪ ሰዎችን ጨምረህ፥ ወደእርሱ ኺደህ፡ ውቅሰህ፥ ይቅር በለው! ታረቀው!" ባላቸው ጊዜ፡ ቅዱስ ጴጥሮስ፡ "በቀን፡ ስንት ጊዜ?" ብሎ ላቀረበው ጥያቄ፡ ከመምህሩ መልሱን ሳያገኝ፡ ያሳመረና የሚሞገስ መስሎት ይመስላል፥ "ሰባት ጊዜን?" ብሎ መጠይቃዊ መልሱን፡ ራሱ በሰጠ ጊዜ፡ መለኮታዊ መምህሩ፡ "ኢይብለከ እስከስብዕ፤ አላ፡ እስከሰብዓ በበስብዕ።"

ማለትም፡ "የለም! 'ሰባት ጊዜ' አልልህም፤ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ።" ብሎ ነው፡ በቍርጥ ቃል የመለሰለት። ይህም ማለት፡ ኃጢአተኛው፡ ካልደከመውና ራሱን መልሶ ካልጎዳው፡ ከፈለገና ከቻለ፡ በቀን፡ አራት መቶ ዘጠና ጊዜም ቢኾን፡ በተለያየ መልክ ቢበድልህና ቢያስቀይምህ፥ ይቅርታም እንኳ ባይጠይቅህ፡ አንተ በበኩልህ፡ ይቅር በለው ማለት ነው። (ማቴ. ፲፰፥ ፲፭-፴፭)

ኪዳናዊ ወንድሜ! እስኪ አስተውለው! እግዚአብሔር፡ ለደግነት እጅግ ደካማና ዳተኛ፥ ለክፋት ግን፡ እጅግ ብርቱና ችኩል የኾነው፡ ፍጡሩ ሰው፡ ይህን ኹሉ እንደማያደርገው፥ ሊያደርገውም እንደማይፈልግ፥ እንደማይችልም እያወቀ፡ ይህን የመሰለ ሕይወታዊ መመሪያን፡ ለዚሁ ሰብአዊ ፍጡሩ ከሰጠ፡ ደግነት፡ ፍጹም ባሕርዩ የኾነው፥ ክፋት ግን በባሕርዩ የሌለው፡ እርሱ እግዚአብሔርማ፡ ያን፡ በወገኑ ላይ፡ በደልን፥ በፈጣሪውም ላይ ኃጢአትን በሚፈጽመው ሰው ላይ፡ በእርሱ በኩል ስለሚያደርገው ድርሻ፡ ምን ማለቱ ይመስልሃል?

**"'ንስሓ!' ከክፉ ወደደግ፥ ከሓሰት፡ ወደእውነት፥ ከጥፋት፡ ወደሕይወት፡ በእርግጥ መመለስ ስለኾነ፡ ለራሱ ሲል፡ ይህን የንስሓ ሥርዓት ይፈጽም፤ ይህን ባያደርግ እንኳ፡ በእኔ በኩል፡ ፈጽሜ ይቅር ብዬዋለሁ!" ማለቱ እኮ ነው እግዚአብሔር።**

ታዲያ! ስለዚሁ ታላቅ እግዚአብሔራዊ ቸርነት፡ ሰዎች፡ "በእግዚአብሔር እናምናለን!" የሚሉት ጭምር፡ ምን እያሉ ነው? ከሚሉት፤ ከብዙው መካከል፡ አንዱን ብቻ ልግለጽ፦ "አዎን! በየቀኑ፡ ኃጢአትን እየሠራ፥ ፍትወተ ሥጋውን እያረካና የፈለገውን በደል እየፈጸመ፡ 'ገና ለገና፡ ይህን ኹሉ ክፋትና ጥፋት፡ በንስሓ ስርየት አስወግደዋለሁ' ለሚለው፡ ይህን ለመሰለው ሰው፡ የለም! ይህ መለኮታዊ ልግሥና፡ ፈጽሞ አይገባውም!" ነው እኮ የሚሉት። እንዲህ በማለት፡ በእየግላቸው፡ የእየራሳቸውን ፍርድ ሰጥተው፥ በማኅበርም፡ የራሳቸውን፡ ሰብአዊ ሕግና ድንጋጌ አቁመው፡ እግዚአብሔርና እናቱ፡ ለዚያ ወንድና ለዚያች ሴት፡ በነጻ የሰጡትን፡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እስከመልከል የደረሱ አይደለም? አዎን! ከለከሉት እኮ። ታዲያ! ለዚህ ለሰዎች ድርጊት፡ ምን እንላለን?

ለመኾኑ፡ የእግዚአብሔር አማኝ ኾኖ፡ ከዓቅሙ በላይ ካልኮነ በቀር፡ በክፋቱና በበደሉ፥ በጥፋቱና በኃጢአቱ፡ ያን ያህል የሚንደላቀቅ ሰው ከቶ ይኖራልን? እግዚአብሔርን ክዶ፥ ራሱን ፈጽሞ ሰይጣን በማድረግ፡ ለዲያብሎስ ባርነት ያደረ ካልኾነ በቀር፡ በእግዚአብሔር የሚያምን ሰው፡ ስለኃጢአትና ስለንስሓ፡ እንደዚያ ያስባልን? ለምን ብሎ? ምን ቸግሮት? ስለሰብአዊ አስተሳሰባችን ኹኔታ፡ እኔ፡ እንዲህ አልሁ እንጂ፡ በእግዚአብሔርማ በኩል፡ በእናቱና ሰው በኾነው ልጃቸው፡ በመሢሕ ኢየሱስ ቤዛነት፡ ሰዎች፡ "ያ የንስሓ ልግሥና አይገባውም!" የተባለውን፡ እንደዚያ ያለውን ደልቃቃና ጕሥቋላ ሰውም እንኳ፡ ከላይ እንዳመለከትሁት፡ ይቅር ብሎታል።

ኃጢአትን ይቅር ማለት ልማዱ የኾነውና ይኸው ርኅራኄው፡ ለጨካኞች ሰዎች የሞት ፍርድ ያበቃው ጌታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ በዚህ ረገድ፡ "ኢትኰንኑ፤ ከመ ኢትትኰነኑ! እስመ በኵነኔ ዘኰነንክሙ፡ ትትኴነኑ አንትሙ። ወበመስፈርት ዘሰፈርክሙ፡ ይሰፍሩ ለክሙ። ለምንት ትሬኢ ሐሠረ፡ ዘውስተ ዐይነ እኁከ? ወኢትሬኢ ሠርዌ፡ ዘውስተ ዐይንከ? ኢታቤይንኑ? ወእፎ ትብሎ ለእኁከ፡- 'ኅድግ! አውጽእ ሐሠረ፤ እምውስተ ዐይንከ!' ወናሁ ሠርዌ፡ እምውስተ ዐይንከ። አ መደልው! አውጽእ ቅድመ፡ ሠርዌ፡ እምውስተ ዐይንከ፤ ወእምዝ፡ ትሬኢ፡ ለአውጽኦ ሐሠር፡ ዘውስተ ዐይነ እኁከ።"

ማለትም፡ "እንዳይፈረድባችሁ፡ አትፍረዱ! በፈረዳችሁበት ፍርድ፡ እናንተም፡ ይፈረድባችኋልና። በሰፈራችሁበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል። በወንድምህ ዓይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ለምን ታያለህ? በራስህ ዓይን ውስጥ፡ ያለውን ግንድ ግን፡ ስለምን አትመለከትም? አታስተውልምን? ደግሞስ፡ እነሆ! በራስህ ዓይን ውስጥ፡ ግንድ እያለ፡ ወንድምህን፡ 'በዓይንህ ውስጥ ያለውን ጉድፍ እንዳወጣልህ ፍቀድልኝ!' እንዴት ልትለው ይቻልሃል? አንተ ግብዝ! አስቀድመህ፡ በራስህ ዓይን ውስጥ ያለውን ግንድ አውጣ! ከዚያ በኋላ፡ በወንድምህ ዓይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ለማውጣት አጥርተህ ታያለህ።" ብሎ የተናገረው ቃል፡ እዚህ ላይ ሊዘከር፡ አግባብ ይኾናል።

ሠሪውና ባለቤቱ እርሱ ራሱ ብቻ ስለኾነ፡ በፍጥረቱ ኹሉ ላይ፡ በሰው ላይ ጭምር የሚፈርድ፡ እግዚአብሔር ብቻ ነውና። ሰው፡ በሰው ላይ ሊፈርድ፡ መብቱና ችሎታው፥ ሥልጣኑና ኃይሉም የለውም፤ አልተሰጠውምም። (ማቴ. ፯፥ ፩-፭።)

ኪዳናዊ ወንድሜ ሆይ! ሌሎቹን፡ ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውጪ የኾኑትን፡ የሰው ወገኖች ኹሉ፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" የሚሉትን ሓሰተኞች ጭምር እንተዋቸውና፡ እየራሳችንን፡ "ኪዳናዊና ኪዳናዊት ነን!" የምንለው፡ እኛ፡ እስኪ! እርስ በርሳችን እንጠያየቅ? ለመኾኑ፡ አንተ ማነህ? እኔስ ማነኝ? አንተና እኔ፡ ከቅዱስ ጴጥሮስ እንበልጣለንን? ከእርሱ በባሰ ኹኔታ፡ "እንዴ! ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! ይኼ ሰባ ጊዜ ሰባቱማ ይበዛል! አይ! ይህማ አይኾንም።" ልንለው ነውን? ከሌሎቹ ሓዋርያት መካከል፡ ኹሉም፡ ገና፡ እንደማናቸውም፡ ክፉና ጨካኝ እንደኾነው ሰው፡ በዚያው በሥጋዊው አእምሮአቸው የሚያስቡ ነበሩና፡ "እንዴ! ይኼ ጴጥሮስ፡ ምን መኾኑ ነው? ምንስ ማለቱ ነው? እንዴት፡ ይህን ያህል አብዝቶ፡ 'ሰባት ጊዜ!' ይላል!" ብለው፡ በየልባቸው ያሰቡ፡ ምናልባት ይኖሩ ይኾናል እኮ። አይታወቅም።

አዎን! በዚህ ጉዳይ፡ መምህራቸው፡ በመጨረሻ፡ በቍርጥ ውሳኔው ለነገራቸው ቃል፡ ኹሉም፡ ምንም ዓይነት መልስ እንዳልሰጡት ይታወቃል። ይኹን እንጂ፡ ስለጋብቻ ጉዳይ ተነሥቶ በተነጋገሩበት፡ በሌላው ጊዜ፡ ሙሴ፡ ምንም እንኳ፡ በአይሁድ ክፋት ምክንያትም ቢኾን፡ ያደረገው ማሻሻል፡ ትክክል እንዳልኾነ በመግለጽ፡ ጥንቱኑ እግዚአብሔር በሠራው ሥርዓት ግን፡ መፋታት እንደማይገባ አብራርቶ ሲነግራቸው፡ "**እመሰ፡ ከመዝ ውእቱ ሥርዓተ ብእሲ ወብእሲት፡ ኢይርቱዕ ያውስቡ።**"

ማለትም፡ "የባልና ሚስት ሥርዓት፡ እንዲህ ከኾነ፡ ጋብቻ **አይጠቅምም!**" ብለው፡ የሰውኛ ብያኔያቸውን ያስታወቁት፡ እኒሁ ደቀ መዛሙርቱ፡ አኹንም፡ በዚህ፡ በይቅርታ ነገር፡ በየልባቸው፡ "አንዳች ቅሬታ ሳይኖራቸው ይቀራል!" ብሎ ማሰብ አዳጋች ይኾናል። (ማቴ. ፲፱፥ ፲።)

ታዲያ! እኛስ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት! ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው፡ እየራሳችንን፡ "ለዚህ ምንነታችንና ማንነታችን አብቅተናል!" ካልን በኋላ፥ ነገር ግን፡ እንዲህ ኾነን ሳንገኝ በመቅረታችን ምክንያት፡ እንደእርሱ፡ እንደእግዚአብሔር ማሰብ፥ መናገርና ማድረግ የተሳነን ከኾንን፡ እርሱን፡ ፈጣሪያችንን፡ "ለምን እንዲህ አደረግህ?" ብለን ልንጠይቀው፥ ወይም፡ "እንዲህ ማድረግ አልነበረብህም!" ብለን ልንበይንበት የሚያስችለን፤ ምን ዓቅምና መብት ይኖረናል? "ለኪዳናዊነቱ፡ ገና ያልበቃን መኾናችንን ተገንዝበን፡ እንደገና፡ እየራሳችንን፡ በጥልቅ መመርመር፡ በብርቱ የሚያስፈልገን ከመኾኑ በቀር፡ ጥያቄውን ልናቀርብለት፥ ብይንም ልንሰጥበት፡ ምንም ዓይነት ዓቅምና መብት፡ ከቶ የለንም።

ስድስተኛው፡ የእግዚአብሔር ባለቃል ኪዳን የኾነው ቅዱስ ዳዊት፡ ታማኝ አገልጋዩን፡ ኢትዮጵያዊዉን፡ ኦርዮን፡ አንዲት ኢትዮጵያዊት፡ የሕግ ሚስቱን፡ ቤትሳባን ቀምቶ፡ ከእርሷ፡ ልጅ መውለድን ብቻ ሳይኾን፡ እርሱን ባሏን፡ በግፍ ካስገደለው በኋላ፡ እርሷን፡ በሚስትነት አግብቶ፡ ከእርሷ፡ የመጀመሪያ ወንድ ልጅን፥ ከዚያም፡ እንደገና፡ ሰሎሞንን መውለዱ ይታወቃል።

ታዲያ፡ ያን የመሰለ አሠቃቂ ኃጢአትን የፈጸመ ንጉሥ ዳዊት፡ በዚህ ኹኔታ ካገባት ኢትዮጵያዊት ቤትሴባ ከተወለደው፡ ከልጁ፡ ከሰሎሞን፡ የቃል ኪዳን ዘሩንና ለድንግል ማርያም አርአያዋ የኾነችውን ጽላተ ኪዳን፡ ወደኢትዮጵያ ለመስመጣት፡ የእግዚአብሔር መሣሪያ የኾነችው፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ ወደኢየሩሳሌም የመኋዟ፥ ደግሞም፡ ከዚህ የትውልድ ሐረግ የተወለደችው፡ ድንግል ማርያም፡ ኢትዮጵያ መኾኗና ከእርሷ፡ መሢሕ ኢየሱስ፡ በኢትዮጵያዊነት፡ የመወለዱም ነገር፡ ምን ይረቅ! ምን ይደንቅ!

ዳዊት፡ ይህን ታላቅ ኃጢአት ከፈጸመ በኋላ፡ ማቅ ለብሶ ዐመድ ነስንሶ፡ የጾመውና ያዘነው፥ የጸለየውም፡ ስለዚሁ ኃጢአቱ፡ ፈጣሪው ይቅር እንዲለው፡ ለንስሓው ሳይኾን፡ በዚሁ ኃጢአቱ የተፀነሰው ሕፃን፡ ከሞት እንዲድንለት መኾኑ፡ ዝክረ ነገሩ ያስረዳል። እግዚአብሔር፡ "ረከብክዎ ለዳዊት ገብርየ፤ ብእሴ ምእመነ ዘከመ ልብየ።"

ማለትም፡ "አገልጋዬ የሚኾን፡ ዳዊትን አገኘሁ፤ እርሱ፡ ልቤ እንደምትሻው የኾነ፡ የታመነ ሰው ነው።" ብሎ የተናገረለት፡ ይኸው ነቢዩ ዳዊት፡ ፈጣሪው፡ እጅግ ርኅሩኅና መሓሪ ይቅር ባይና ኃጢአቱን የማይቆጥርበት መኾኑን ያውቃል። እንዲሁም፡ ያ በውስጡ ያለው ፍትወተ ሥጋ፥ እንዲሁም፡ ዘሩና ስሜቱ፡ እግዚአብሔር፡ በመልካምነቱ የፈጠረውና የሠራው መልካም መኾኑንም ያውቃል፤ ያምናልም። ለምን፡ ያ ኹሉ፡ በእርሱ እንዲፈጸም፥ ለምንስ፡ ከዓቅሙ በላይ ግድ እንደኾነበት፡ ደኅና አድርጎ ያውቃል። ይህንም እውቀት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ይጋሩታል።

ይኸው ዳዊት፡ ስለዚህ በደሉና ግፉ፡ እግዚአብሔር፡ በእርሱ ላይ የወሰነውን ቅጣት ለመቀበል፡ ፈቃደኛና ዝግጁ ኾኖ፡ የጀመረውን ዓላማ፡ ከግብ ለማድረስ፡ ወደፊት ከመቀጠል በቀር፡ ስለንስሓው፡ ምንም ያደረገው ነገር እንደሌለ፤ ዜና መዋዕሉ ይናገራል። ይህንም እውነታ፡ ከቤትሳባ የወለደው ሕፃን ልጁ ሲሞትበት፡ እንደኦሪታውያኑ ልማድ፡ ማቅ ለብሶና ዐመድ ነስንሶ፡ መሬት በመተኛት የጀመረውን፡ የጾሙንና የኀዘኑን ሱባኤ አቁሞ፥ ወደዐልጋውና ወደዙፋኑም ተመልሶ፡ የተለመደ ኑሮውንና ተግባሩን በመቀጠል አሳይቷል።

"ብፁዕ ብእሲ፡ ዘኢኈለቈ እግዚአብሔር ኃጢአቶ! ...ብፁዓን እለ ተኀድገ ሎሙ ኃጢአቶሙ፤ ወእለ ኢሓሰበ ሎሙ ኵሎ ጌጋዮሙ።"

ማለትም፡ ""እግዚአብሔር፡ ኃጢአቱን የማይቈጣጠረው ሰው ብፁዕ (ዕድለኛ) ነው። ...ኃጢአታቸው የተተወላቸው (የተሰረየላቸው)፥ በደላቸውም (ጥፋታቸውም) ኹሉ ያልታሰበባቸው ሰዎች፡ ብፁዓን (የታደሉ) ናቸው።" ከተባሉት እውነተኞች ሰዎች መካከል አንዱ፡ ይኸው ቅዱስ ዳዊት መኾኑን፡ ይኸው፡ በገሃድ መመልከት ነው። አስተሳሰባቸውና እምነታቸው፡ እንደዚህ ኪዳናዊ የኾኑት፡ እውነተኞቹና ታማኞቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያትም፡ ዕድል ፋንታቸው፥ ጽዋ ተርታቸው፡ ይኸው ብፅዕና ነው።

ወደኢትዮጵያ ለመጣው፡ ለዚህ፡ ለመለኮታዊው የቃል ኪዳን ዘር የተከፈለው ኢትዮጵያዊ መሥዋዕትነት፡ የቱን ያህል ከባድ መኾኑን፡ በማስተዋል መመልከት ነው፦ ይህም፡ ፩ደኛ፡ ራሱ፡ የኢትዮጵያዊው የኦርዮና የኢትዮጵያዊቷ የቤትሳባ ኢትዮጵያዊ ጋብቻ፣ ፪ተኛ፡ የኢትዮጵያዊው የኦርዮን ንጹሕ ደም፣ ፫ተኛ፡ ዳዊት፡ ከኢትዮጵያዊቷ ቤትሳባ የወለደው፡ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሕፃን ቅሥፈት ናቸው።

እኒህን ቤዛዎች የሚያካትተው፡ ይህ፡ የዳዊት የቃል ኪዳን ዘር፡ ንግሥት ማክዳ፡ ከዳዊት ልጅ፡ ከሰሎሞን፡ ምኒልክን ያስገኘችበት ልደት፡ በድንግልናዋ እንጂ፡ በመገሠሥ እንዳልኾነ የሚያረጋግጠው እውነታ፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥ እንዳልተጨመረ ሊታወስ ይገባል።

ከዚህ፡ ከዳዊትና ከቤትሳባ ዝክረ ነገር ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን፡ ሌሎቹን ብዙዎች የእግዚአብሔር ሰዎች፡ በምሳሌነት ማቅረብ ይቻላል። ለጊዜው ግን፡ ከዚህ ርእሰ ነገር ጋር አግባብነት ያላቸውንና ዜናቸው በስፋት የሚነገርላቸውን፡ ጥቂቶቹን ብቻ በስማቸው ብቻ እጠቅሳቸው ዘንድ አስፈላጊ ይኾናል። እነርሱም፡ ኢትዮጵያና የእግዚአብሔር እናት ለኾነችው ለድንግል ማርያም፥ ለልጇም ለመሢሕ ኢየሱስ የዘር ሓረግ ግንዶች ለመኾን የተመረጡትና የበቁት፥ እንዲሁም፡ ኢትዮጵያዊነትን ለሚያስገኘው፡ ለሴም፥ ለካምና ለያፌት ዘሮች ውሕደት መዛሪያዎች የኾኑት፡ ከዚህ የሚከተሉት ሴቶች ናቸው፡-

፩ደኛ፡ "እስራኤል" ከተባለው፡ ከያዕቆብ ልጅ፡ ከይሁዳ፡ ፋሬስንና ዛራን የወለደችው፥ ትዕማር ናት፤ እርሷም፡ የዚሁ የይሁዳ፡ የኹለት ልጆቹ ሚስት የነበረችው ናት።

፪ተኛ፡ ከሰልሞን፡ ቦኤዝን የወለደችው ረዓብ (ራኬብ) ናት፤ እርሷም፡ በኢያሪኮ ከተማ፡ የታወቀች ጋለሞታ (ሴትኛ ዐዳሪ) የነበረች ናት።

፫ተኛ፡ ከቦኤዝ፡ የቅዱስ ዳዊትን አያት፡ ኢዮቤድን የወለደችው፡ ሞዓባዊቷ ሩት ናት፤ እርሷም፡ የአብርሃም ወንድም፥ በብቅዓቱም፡ የእግዚአብሔር መላእክት እቤቱ ገብተው፡ ከሰዶምና ገሞራ እሳት፡ ከኹለት ሴቶች ልጆቹ ጋር ያዳኑት ሎጥ፡ ከእነዚሁ ሴቶች ልጆቹ ከወለዷቸው ከኹለት ወንዶች ልጆች፡ "ሞዓብ" ከተባለው የተወለደች ናት። (ማቴ. ፩፥ ፩-፲፮።)

ኪዳናዊ ወንድሜ! የተመረጡና የተለዩ የተባሉት፡ ሴማውያቱ፡ እነሣራ፥ ርብቃና ራሔል፡ ስማቸው ሳይወሳ፡ "የተናቁና የተጠሉ የአሕዛብ ወገኖች፥ የተረገሙና የረከሱ ኃጢኣተኞች!" የተባሉ፡ እኒህ ሴቶች፡ የእግዚአብሔርን ልጅ፡ መሢሕ ኢየሱስን የወለደችው፡ የኢትዮጵያዊቷ ድንግል ማርያም፡ አያቶች፥ ቅድመያቶችና ምዝላቶች ለመኾን የመብቃታቸውን ነገር፡ ምን እንለዋለን? እግዚአብሔር፡ ይህን፡ ለምን አደረገ? ይህ ነገር፡ ለእኛስ ምን መልእክት አለው? ለምንወያይበት ጉዳይ፡ በቂ የኾነውን መልስ የሚሰጠን ነው።

አዎን! "ኀበ ሀለወት ብዝኀት ኃጢኣት፡ በህየ ትበዝኅ፡ ጸጋ እግዚአብሔር!"

ማለትም፡ "ኃጢኣት በበዛች ቍጥር፡ የእግዚአብሔር ጸጋም በዚያው መጠን፡ ትበዛለች!" እያልን፡ በየዕለቱ የምንጸልየው፡ ምን ማለታችን ይኾን? ይህ እግዚአብሔራዊ የእውነት ቃል፡ በሰኞው፡ የውዳሴ ማርያም ጸሎት ውስጥ የሚገኝ ኾኖ፡ ዘወትር የምንደግመውና የምንጸልየው ሲኾን፡ የዚሁ ጸሎት፡ መልእክቱ፥ ወይም፡ ትርጉሙ ሳይገባቸው የሚጸልዩት አሉ ማለት ነውን? አዎን! አሉ።

ታዲያ! "እናምናለን!" እያሉ፡ የሚሉት ሌላ፥ የሚኾኑትና የሚያደርጉት ግን፡ ሌላ፡ እንዴት ሊኾን ይችላል!? አይችልም። መለኮታዊው መምህራችን፡ "ግብዝነት!" ያለው ይኼን ነው። በጊዜው በነበሩት፡ "የእግዚአብሔር ሃይማኖተኞችና መንፈሳውያን አገልጋዮች ነን!" በሚሉት ሰዎች ዘንድ፡ ሲፈጸም ባየው ድርጊት፡ በተግሣፅ መልክ የነቀፈውና የወቀሰው፡ ታዲያ! ይህን የመሰለውን፡ የግብዝነት ጠባይና ግብር አይደለምን? ነው እንጂ።

በአረማውያን ዘንድ ሳይቀር፡ በአንድ ወገን፡ "ክርስቲያኖች ነን!" እያሉ፡ በራሳቸው የሚመጻደቁትን፡ እንግሊዞችን ያሳፈረ፥ ራሱን ክርስትናንም አጠያያቂ ያደረገ፥ ለይፋ ግብዝነትም የዳረገ፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ ክርስቲያናዊ ምግባርን በመፈጸም፡ የሰዎች ሃይማኖት፡ እንኳን፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ በሰውም ዘንድ የሚታወቀው፡ በስም ሳይኾን፡ በፍሬው መኾኑን ያረጋገጠ፡ የሕንዳዊዉን የእነማኀተማ ጋንዲን የመሰለ ገድል መኖሩ፡ ምንጊዜም ሊዘከር ይገባዋል።

ዛሬም፡ እየራሳቸውን፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" ብለው የሚጠሩ፡ የዚህ ትውልድ ወገኖች፡ "የእግዚአብሔር ሃይማኖተኞችና መንፈሳውያን አገልጋዮች ነን!" የሚሉት ጭምር፥ በአረማውያኑና በአይሁዳውያኑ፥ በእስላማውያኑና በክርስቲያናውያኑ፥ በኹሉም ዘንድ ሳይቀር፥ በማናቸውም ረገድ፡ ያለባቸው ችግር፡ ይኸው አይደለምን? ነው እንጂ።

በእኛ፡ በኪዳናውያንና በኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ ግን፡ እንዲህ ሊኾን አይችልም፤ ሊኾንም አይገባም። ምክንያቱም፡ በጸሎት መልክ፡ ዘወትር የምንደግመው፡ ያ፡ ከላይ የተጠቀሰው፡**"ኀበ ሀለወት ብዝኀት ኃጢአት፡ በህየ ትበዝኅ፡ ጸጋ እግዚአብሔር!"**

ማለትም፡ **"ኃጢአት በበዛች ቍጥር፡ የእግዚአብሔር ጸጋ፡ በዚያው መጠን፡ ትበዛለች!"** የሚለው ቃል፡ የእግዚአብሔር፡ ፍጹም ፍቅርና ቸርነት፡ በግብር የተገለጹበት፡ መለኮታዊ ትንግርት የኾነው እውነት፡ የዛሬ ፪ሺ፯ ዓመት፡ በሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል አንደበት በተሰማው የምሥራች ቃል፡ በገሃድና በግዘፍ፥ ለአንዴና ለዘለዓለም፡ ተፈጽሞና እውን ኾኖ የታየ፥ ከዚያም ወዲህ፡ በዚያ ኹኔታው የቀጠለ በመኾኑ ነው።

ይኸውም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ መሢሕ ኢየሱስ፡ ወደዚህ ዓለም፡ በሰውነት መምጣት ያስፈለገው፡ ለምን እንደኾነ፡ የተናገራቸው፡ ብዙዎቹ ቃላቱና ምሳሌዎቹ፡ በሚበቃ ያስረዳሉ፤ ያስገነዝባሉ፤ ያሳምናሉም። ከእነዚህ መካከል፡ ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸውን፡ **"እስመ ኢመጽአ ወልደ ዕጓለ እመሕያው፡ ዘእንበለ ከመ ይኅሥሥ፥ ወያድኅን፡ ዘተኀጕለ።"**

ማለትም፡ **"የማርያም ልጅ፡ የጠፉውን ሊፈልግና ሊያድን ካልኾነ በቀር፡ ለሌላ ግዳጅ፥ ወይም፡ ዓላማ አልመጣምና።"** የሚለውን፡ አንዱን ብቻ ለማስረጃ ያህል፡ እዚህ ላይ ጠቅሼዋለሁ።

መለኮታዊው መምህራችን፡ ይህን ካለ በኋላ፡ የጠፋውን ቦዘኔ በሚመለከት፡ ስለፍለጋው አካኼድና አግኝቶ ስለማዳኑ ፍጻሜ፡ እንዴት ባለ ኹኔታ እንደሚከናወን፡ በበለጠ አብራርቶታል። ያብራራውም፡ ባለቤቱ እርሱ፡ ሥፍር ቍጥር ከሌለውና እጅግ ተትረፍርፎት ከሚገኘው የሀብቱ ብዛት መካከል፡ የጐደለው፡ አንድ ብቻ ሲኾን፡ ያን ኹሉ የቀረ ይዞታውን፡ እንዳለው ሳይቆጥር፡ ባኖረበት ትቶ፡ የበለጠ ያሰበውና የተጨነቀው፡ ለዚያ፡ ለአንዱ ለጠፋበት ብቻ መኾኑን፥ እርሱንም ፈልጎ ለማግኘት፡ የሌሎችን እርዳታ፥ ወይም፡ መልእክተኝነት ሳይጠይቅ፥ ወይም፡ ሳይሻ፡ ራሱ መምጣት እንዳለበት፥ እስኪያገኘውም ድረስ፡ ማናቸውንም ገድል በመፈጸም፡ እስከመጨረሻው ሊቀጥል፥ ባገኘውም ጊዜ፡ ማናቸውንም ዋጋ፥ ወይም፡ ካሣ በመክፈል፥ እንዲያውም፡ ካስፈለገ፡ ራሱን እስከመሠዋት በሚያደርስ መጠን ቤዥቶ፡ ያን፡ የጠፋውን ሀብቱን መልሶ እጁ ለማግባት መኾኑን በመግለጽ ነው።

ይህንም፡ አከታትሎ በሰጠው ምሳሌያዊ ታሪክ፡ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡- **"ምንተ ትብሉ? እመቦ ብእሲ፡ ዘቦቱ ምእት አባግዕ፤ ወእመ ተገድፈ፡ አሐዱ እምውስቴቶሙ፡ አኮኑ የኀድግ፡ ተስዓ ወተስዐተ፡ ውስተ ገዳም፤ ወየሐውር፣ ይኅሥሥ ዘተገድፎ። ወእምከመ ረከቦ፡ አማን እብለክሙ! ከመ ይትፌሣሕ፡ በእንቲአሁ ፈድፋደ፡ እምተስዓ ወተስዐቱ፡ እለ ኢተገድፉ።"**

ማለትም፡ **"ምን ትላላችሁ? ለአንድ ሰው፡ መቶ በጎች ቢኖሩት፡ ከእነርሱም፡ አንዱ ቢባዝን፡ ዘጠና ዘጠኙን፡ በሜዳ ትቶ፡ ኼዶም፡ የባዘነውን አይፈልግምን? ቢያገኘውም፡ እውነት እላችኋለሁ! ካልባዘኑቱ፡ ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ፡ በእርሱ፡ ደስ ይለዋል።"**

እንዲህ ብሎ፡ በራሱ በኩል ሊፈጽም የወሰነውን ካስታወቃቸው በኋላ፡ አማኞቹና ተከታዮቹ ለኾኑት ደቀ መዛሙርቱ፡ አያይዞ፡ በመጨረሻ ያላቸውን፡ አንተም፥ እኔም፥ ኹላችንም፡ እናውቀው የለምን? ምንድር ነው ያላቸው? ያላቸውማ፡ **"ከማሁኬ፡ ኢይፈቅድ፡ አቡየኒ ዘበሰማያት፡ ከመ ይትኀጐል አሐዱ፡ እምእሉ ንኡሳን!"**

ማለትም፡ **"እንደዚሁ ኹሉ፡ ከእነዚህ፡ ከታናናሾቹ መካከል፡ አንዱ እንዲጠፋ፡ የሰማዩ አባቴ አይፈቅድም።"** የሚለው ቍርጥ ቃሉ ነው። (ማቴ. ፲፰፥ ፲፩-፲፬።)

እንዲህ ባለ መልክ፡ ከክፋታቸውና ከኃጢአታቸው፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ ወደኪዳናዊው ኢትዮጵያዊነታቸው ስለሚመለሱትም ዕድለኞች፡ መሪያችንና መምህራችን፡ ገልጾና አበክሮ ያሳወቀን፡ የምሥራች ቃል አለ። ይህም፡ ከላይ በተጠቀሰው ዓይነት፡ በመለኮታዊው አንደበት የተነገሩት ምሳሌዎችን በማጠቃለል፡ **"እብለክሙ፡ ከመ ከመዝ ይከውን ትፍሥሕት በሰማያት፥ በቅድመ መላእክተ እግዚአብሔር፡ በበይነ አሐዱ ኃጥእ ዘይኔስሕ፡ ፈድፋደ፡ እምነ ተስዓ ወተስዓቱ ጻድቃን፡ እለ ኢይፈቅዱ ይነስሑ።"**

ማለትም፡ "እላችኋለሁ፤ ንስሓ ከማያስፈልጋቸው፡ ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ፡ ንስሓ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ፡ በሰማያት፡ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት፡ የበለጠ ደስታ ይኾናል።" ያለው ነው። (ሉቃ. ፲፭፥ ፩-፴፪።)

ስለዚህ፡ ለቀደሙት እውነተኞችና ታማኞች ለኾኑት ኪዳናውያንና ኪዳናውያት አገልጋዮቹ ሓዋርያት፡ የሰጣቸው ይህ መመሪያ ቃል፡ ለእኛ፡ ለዛሬዎቹ፡ እውነተኞቹና ታማኞቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት "አገልጋዮቹ ሓዋርያት ነን!" ለምንለውም፡ የሚጸና መኾኑን፡ ከመካከላችን የሚጠራጠር ያለ አይመስለኝም። ምናልባት፡ ካለ፡ ራሱን/ራሷን፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እውቀትና ንስሓ ማስተካከል፡ አግባብ ይኾናል።

ከዚህ ምሳሌው በማስከተል፡ ቅዱስ ጴጥሮስን፡ "የለም! አንተ፡ *'በቀን ሰባት ጊዜ ይበቃዋል!'* ብለህ፡ በሰብኣዊ ልግሥናህ የቸርከው ችሮታህ፡ ግድየለህም፡ አይበቃውምና፡ ይኼን የጠፋውን ወገንህን ለማዳን፡ በእኔ ዘንድ፡ ያለው የምሕረት ይቅርታ፡ ወሰን የሌለው ቢኾንም፡ እስኪ፡ በአንተም በኩል፡ እባክህ! በቀን፡ ሰባ ጊዜ ሰባትም ቢኾን፡ ግዴለህም! ይቅር በለው!" ያለው፡ ታዲያ ለምንድር ነው? የጠፋበትን የሰው ዘር፡ በማናቸውም መንገድ፡ ፈልጎ በማግኘት፡ የመጣበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ፡ ምንም የሚያግደውና የሚከለክለው ምክንያት አለመኖሩን፥ ያው፡ ደርሶ እንደታየው፡ ራሱን፡ በቤዛነት፡ ለመሥዋዕትነት እስከማቅረብም ቢኾን፡ የማይመለስ መኾኑን፡ በቅርቡ ላሉት ለተከተሉት አማኞቹ፡ በአጽንዖት ለማስገንዘብ አይደለምን?

ታዲያ! ይህ ማስገንዘቢያ፡ ለእኛም፡ ለዛሬዎቹ እውነተኞችና ታማኞች ኪዳናውያንና ኪዳናውያት አማኞቹ፥ ተከታዮቹና አገልጋዮቹ ጭምር አይደለምን? በእርግጥ፡ ነው እንጂ!

እዚህ ላይ፡ መምህራችን፡ ከዚሁ ጋር በተዛመደ መልኩ ያቀረበውን፡ አወሳው ዘንድ የሚያስፈልግ፥ አንድ ሌላ መለኮታዊ ምሳሌና መመሪያ አለ፤ ይኸውም፡ የአንድ ደግ ባለጸጋ አባት ልጆች የኾኑ፡ የኹለት ወንድማማቾች ታሪክ ነው። ታላቅዬው፡ አባትዬውን የሚመስል በመኾኑ፡ ንስሓ የማያስፈልገው እውነተኛ ሰው (ጻድቅ) ነው፤ ታናሽዬው ግን፡ ከኃጢአቱ ጽናትና ከበደሉ ብዛት የተነሣ፡ በነፍስና በመንፈስ የወለደውን፡ የሰማይ አባቱ ወደኾነው፡ ወደፈጣሪው፡ ቀና ብሎ ለመጸለይ፥ በሥጋ የወለደውን አባቱንም፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ልጁ ተብሎ መጠራት እንኳን እንደማይገባው፡ በራሱ አምኖና ፈርዶ፡ ወደዚሁ ወላጁ ለመመለስ ወሰነ። ከሚጠብቀው ሞት ተርፎ፡ በሕይወት ለመቀጠል፡ ሌላ፡ ምንም ዓይነት ማማረጫ እንደሌለው ሲያረጋግጥ፡ አባቱ፡ ምንም ቢጨክንበት፡ አገልጋይነትን እንደማይነፍገው በማመን፡ ዓይን አውጥቶ፡ በቈራጥነት፡ ወደአባቱ ቤት ተመለሰ። በዚያን ጊዜም፡ በአባቱ በኩል ስለተደረገለት አቀባበል፡ ከቶ፡ እኛ፡ የዛሬዎቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ምን እንላለን?

ያ፡ በእግዚአብሔር የተመሰለው አባትዬው፡ ለአጥፊውና ለበዳዩ ታናሽ ልጁ ስላደረገው ርኅራኄና ምሕረት፥ የሓሴትና የሽልማት ትሩፋትም፡ እንኳንስ እኛ፡ ያ፡ "አባቱን ይመስላል!" የተባለው፡ ታላቁ ልጁ እንኳ፡ የአባቱ ምግባር፡ ወዲያው፡ በትክክል ሊገባውና ሊያስተውለው፥ ሊቀበለውና ሊያምንበት እንዳልተቻለው፡ ከዝክረ ነገሩ እንገነዘባለን። ታዲያ! እንደዚያ፡ እንደታላቁ ልጁ ኹሉ፡ ምናልባት፡ በአስተሳሰባችን፡ እንደእርሱ ኾነን የምንገኝ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ በእኛም መካከል እንኖር ይኾን? ካለን፡ የመንፈስ ቅዱስ መልስ፡ እነሆ!

በጊዜው፡ በአጠገቡ እየተገኙ፡ **"ዝንቱሰ፡ ኃጥኣነ ይትዌከፍ፤ ወይበልዕ ምስሌሆሙ!"**

ማለትም፡ **"ይህስ፡ ኃጢአተኞችን ይቀበላል፤ ዐብሮአቸውም ይበላል!"** እያሉ ላንጐራጐሩበት፥ ገና በሰውኛውና በኦሪታዊው የጭካኔ ቀንበር ተጠምደው ይጐሠቍሉ ለነበሩት፥ እየራሳቸውን ግን ያመጻድቁ ለነበሩት የአይሁድ ሊቃውንትና ካህናት፡ ያቀረበውን መለኮታዊ ምሳሌ፡ ሩኅሩኁና መሐሪው፥ ለጋሡና ፍሡሑ አባት፡ እንዲህ ሲል፡ ለትልቁ ልጁ፡ በተናገረው፡ እውነተኛ የማጽናኛና የማሳመኛ ቃል ደምድሞታል፦ **"ወልድየ! አንተሰ፡ ዘልፈ ሀለውከ ምስሌየ፤ ወኵሉ ዘዚአየ፡ ዚአከ ውእቱ። ወባሕቱ፡ ርቱዕሰ ንትፈሣሕ! እስመ ዝንቱ እኁከ፡ ሞተሂ፤ ወሐይወ፤ ተኀጕለሂ፤ ወተረክበ።"**

ማለትም፡ **"ልጄ ሆይ! አንተማ፡ ይኸው፡ ከእኔ ጋር፡ ሕያው ኾነህ፡ ዘወትር ዐብረኸኝ አለህ፤ የእኔ የኾነውም ኹሉ፡ የአንተ ነው። ነገር ግን፡ ሞቶ የነበረው፡ ይህ ወንድምህ፡ ይኸው ሕያው ኾነ! ጠፍቶም የነበረው እርሱ፡ ይኸው ተገኘ!"** (ሉቃ. ፲፭፣ ፩-፴፪።)

በሃይማኖት ጸሎታችን ውስጥ፡ **"ወነአምን በአሓቲ ጥምቀት ለስርየተ ኃጢኣት።"**

ማለትም፡ **"ኃጢአት በሚሰረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን!"** እያልን፡ ያለማቋረጥ፡ በየዕለቱና በየሰዓቱ የምናረጋግጠው የእምነት አቋማችን፡ ያው፡ እንደሌሎቹ የጸሎት ይትበሃላችን፡ በደመ ነፍስ ብቻ የምናነበንበው እንጂ፡ ገብቶንና ተረድተነው የምንጸልየው አለመኾኑ፡ በሃይማኖታዊው የምግባር ፍሬያችን፡ በገሃድ የሚታይ ነው።

ይኸውም፡ ስለኃጢኣት ያለን አስተሳሰብ፡ አኹንም፡ ያው ክፉው ቀምበርነቱ፥ ገዢነቱና አስፈሪነቱ እንጂ፡ በጥምቀታችን ጊዜና ከዚያ በኋላ፡ ኃጢኣት፡ ከእያንዳንዳችን ጥሙቃንና ጥሙቃት፡ ለአንዴና ለዘለዓለም፡ በስርየት የተወገደ መኾኑ አይደለም። ከዚህ የተነሣም፡ ፈጣሪያችንና አምላካችን ወደኾነው፡ ወደአባታችን እግዚአብሔር እና ኢትዮጵያ አገራችንና ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ወደኾነችው፡ ወደእናታችን፡ ድንግል ማርያም የሚያቀርበንን፡ ቅዱስ ቍርባንን ከመቀበል ይልቅ፡ ከእርሱ እንድንርቅ የሚያደርገን ኾነ።

በዚህ አንጻር፡ በማሕፀን ብቻ ሳይኾን፡ ተወልደን ፵ እና ፹ ቀን ሲኾነን ከተጠመቅን ጀምሮ፡ መሢሕ ኢየሱስ፡ ከድንግል ማርያም በወረሰው ሰውነት፡ በመስቀል ተሰቅሎ፡ በቆረሰው ሥጋውና ባፈሰሰው ደሙ፡ ከቀምበሩና ከባርነቱ፥ ከእሥራቱና ከፍዳው ኹሉ ተፈትተንና ነጻ ወጥተን፥ ለቅዱስ ቍርባንም የበቃን ኾነን እንገኛለን። እውነታው፡ ይኼ ኾኖ ሣለ፡ ነገር ግን፡ ይህ ኹሉ የተትረፈረፈ መለኮታዊ ቸርነት፡ ገና፡ በምንም እንዳልተደረገ ተቆጥሮ፡ ወገኖቻችን፡ የወንድ ዘርና የሴት የወር አበባ፥ ጋብቻና መውለድም፡ በእየራሳቸው፡ "ኃጢኣት፥ መርገምና ርኵሰት" ተብለው፡ በዐዋጅ በታወቁበት ኅብረተሰብ መካከል፡ እነሆ፡ በዚሁ፡ በኃጢኣት ቀንበር፥ በመርገም እሥራትና በርኵሰት ጠንቅ እየማቀቁ መቀጠላቸው ይታያል።

በወገኖቻችን ላይ፡ በሥጋና በነፍስ፥ በመንፈስም፡ እየደረሰባቸው ያለውን፡ ይህን ሥቃይና ጕሥቍልና ማየት፡ አዎን! ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ እጅግ ከባድ ትካዜ ነው። ይኹን እንጂ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ይህ ኹሉ ችግር፡ በቅርቡ እንደሚወገድ ተስፋችን ጽኑ ነው።

ማብራሪያዬን ለመደምደም፡ እዚህ ላይ፡ የእግዚአብሔር አብና የኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም ልጅ፡ ኢትዮጵያዊው መሢሕ ኢየሱስ፡ ፍጥረተ ዓለሙን፡ ከክፉው ጭቆና፥ ከሓሰቱ ግዛትና ከሞት መራራ ጽዋ ነጻ አውጥቶ ሊያድን፡ በመስቀል ላይ ተቸንክሮና ዕርቃኑን ተዘርግቶ፡ ቤዛ ኾኖ የሚሠዋለት፡ ይኸው ፍጥረተ ዓለም፡ በጠራራ ፀሓይ እያየው፡ ሥጋውን እንደእርድ ከብት እየተለተሉና ደሙን እንደጕርፍ እያፈሰሱ፡ ወደር በሌለው ጭካኔ ለሚያሠቃዩት ግፈኞች እንኳ ሳይቀር፡ የተናገረውን፡ ከመጨረሻ ቃሎቹ መካከል፡ አንዱን እጠቅሳለሁ፤ እርሱም፦

"አባ! ሥረይ ሎሙ! እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ!"

ማለትም፡ "አባት ሆይ! በእኔ ላይ እያደረጉ ያሉትን፡ ይህን ኹሉ ግፍ የሚፈጽሙት፡ የእኔን ማንነትና የመጣሁበትን ዓላማ፡ በእውነተኛ መልኩና ባሕርዩ ባለማወቅ እንጂ፡ ቢያውቁ ኖሮ እኮ፡ አያደርጉትም ነበርና፡ እባክህ፡ ስለእናቴና ስለእኔ ስትል፡ በታወቀው የምሕረት ቃል ኪዳንህ፡ ይህን ኃጢኣታቸውን፡ ይቅር በላቸው!" የሚለው ነው።

ለእኛ፡ ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ መልካም አርአያ ለመኾን፡ ለእነዚያ፡ ለሚያሠቃዩት የክፋትና የግፍ ሰዎች፡ ይህን የመሰለውን፡ የምሕረት ይቅርታን፡ በትስብእታዊ ባሕርዩ ለምኖና አማልዶ፡ ከመለኮታዊ ባሕርዩ ጋር እንዲህ አስታረቀ።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ይህን ስርየት ባስገኘባት፡ በዚያችው ጊዜ ደግሞ፡ ሌላ ተመሳሳይ፥ እንዲያውም፡ የበለጠ፡ የመሓሪነቱንና የይቅር ባይነቱን ቸርነት አከታትሎ ፈጸመ። ይኸውም፡ እዚያው፡ እመስቀሉ ላይ እንዳለ፡ ከዚህ የምልጃ ቃሉ፡ ወዲያው በማስከተል፡ ያደረገው፡ የመሓሪነቱ ታላቅ ሥራ ነው።

ያም፡ በቀኙ ለተሰቀለውና ጥፋቱን በሰው ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ አምኖ፡ የስቅላትና የሞት ፍርድ ቅጣቱን እየተቀበለ ላለው፡ ፍጹም ኃጢአተኛ ለኾነው ወንበዴ የተደረገው ነው።

ይኸው ወንበዴ፡ በግራ በተሰቀለው ጓደኛውና በእርሱ መካከል የተሰቀለው፡ ኢየሱስ መሢሕ፡ ማን እንደኾነ አውቆ፡ "ተዘከረኒ እግዚኦ! አመ ትመጽእ በመንግሥትከ!"

ማለትም፡ "ጌታ ሆይ! በመንግሥትህ ተገልጠህ በምትመጣበት ጊዜ፡ አቤቱ አስበኝ!" ባለው ጊዜ፡ ጌታችን መሢሕ ኢየሱስ፡ "አማን እብለከ! እመን ፈድፋደ፣ ከመ ዮም፡ ትሄሉ ምስሌየ ውስተ ገነት!"

ማለትም፡ "እውነት እልሃለሁ፣ ዛሬ፡ ከእኔ ጋር፡ በገነት እንድትኾን፡ ፈጽመህ እመን!" አለው። (ሉቃ. ፳፫፥ ፵፪-፵፫።)

በቅዱሱ ኪዳን፡ እውነተኛዎቹና ታማኞቹ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በዚህ፡ በእግዚአብሔር የእውነት ቃል ታንጸው፡ የእየራሳቸውን ኪዳናዊ ሕይወት ይኖራሉ። እንደመሪያቸውና እንደመምህራቸው፡ ምግባራዊ መርሑ፡ በማንም ፍጡር ወገናቸው ላይ፡ የእየራሳቸውን ፍርድ ከመስጠት ታቅበው፥ ከዚህ ይልቅ፡ በሰብአዊ አእምሮ ሊመጠን የማይቻለውን፡ የፈጣሪያቸውንና የቅድስት እናቱን፡ የምሕረት ቃል ኪዳን፡ እንደቅዱሳን መላእክት፡ በመንፈስ ቅዱሳዊው አእምሮአቸው እያዩ በማድነቅ፡ ሌሎቹንም፡ የጠፉትን፡ የሰው ወገኖች፡ ካሉበት አሠቃቂ ጕሥቍልና ነጻ እንዲወጡ፥ ለዚሁ፡ ለኪዳናዊው ኢትዮጵያዊ ምንነትና ማንነትም እንዲበቁ፡ የተቻላቸውን የተልእኮ አገልግሎታቸውን፡ በያሉበት፡ ያለንፍገት፡ ለኹሉ ያበረክታሉ።

ይህም የተልእኮ አገልግሎታቸው፡ እነዚያን፡ በተለይ በድክመታቸውና በአላዋቂነታቸው ምክንያት፡ በክፋት ባርነት፥ በኃጢአት ቀንበርና በሞት ፍዳ ተተብትበው እየማቀቁ ለሚገኙት የተፈጥሮ ወገኖቻቸው፡ ለወንዶቹም፥ ለሴቶቹም፡ በእግዚአብሔር እውቀት አማካይነት፡ የእግዚአብሔርን እውነት እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው።

በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ ጥንቱኑም ኾነ በመካከሉ፥ ዛሬና ወደፊትም፡ ሲካኼድ የኖረው፥ እየተካኼደ ያለውና በመካኼድ የሚቀጥለው፡ የኪዳናውያንና የኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ተልእኮ፡ የመለኮታውያን መሪዎቻቸውን ፈለግ ተከትለውና እየተከተሉ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያሉትን፡ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ እያንከባከቡ መጠበቅ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ የጠፉትን የሰው ልጆች፡ ፈልጎ ማግኘትና "የእግዚአብሔር ልጆች" ወደሚኾኑበት፡ ወደቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት መመለስ መኾን እንዳለበት፡ ለአንተ፣ ለኪዳናዊው ወንድሜና ክህነታዊ ባልደረባዬ፥ አንተንም ለመሰሉት፡ ለእኛዎቹ ኹሉ፡ አበክሬና አጠንክሬ ማሳሰብ እወድዳለሁ።

ታዲያ! በዚህ ኹሉ፡ አንተም፥ እኔም፥ ኹላችንም፡ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን፡ ልንሰማና ልንቀበል፥ ልንከተልና ልንፈጽም የሚገባን፡ ከሰብአዊው አብራክና ማሕፀን ጀምሮ፡ በየልቦናችን ጽላት ላይ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የተጻፉትን፡ የእርሱን፡ የመለኮታዊ መምህራችንን ቃልና መመሪያ ብቻ እንጂ፡ የፍጡር የኾነውንና በፍጡራን የተጻፈውን ቃልና መመሪያ እንዳልኾነ፡ በፍጹም እንደምንስማማበት አምናለሁ።

በአንተ በኩል የገለጽኸው አስተያየት፥ በእኔም በኩል ያበረከትሁት ማብራሪያ፥ ለኪዳናውያት እኅቶቻችንና ለኪዳናውያን ወንድሞቻችን፥ ለአንባቢዎቻችን ጭምር፡ ትምህርታዊ ረብኅ ጥቅም ሊኖረው እንደሚችል በማመን፡ የኹለቱንም ጽሑፎች፡ ቅጂያቸውን የምልክላቸው መኾኑን እንድታውቀው ይኹን!

በአባታችን በቅዱስ እግዚአብሔር ሰላም፥ በእናታችን፡ በቅድስት ኢትዮጵያ ፍቅር፡ ከኪዳናዊው ቤተሰብህ ጋር ደኅና ኹን!

ኅዳር ፳፯ ቀን፥ ፳፻፯ ዓመተ ምሕረት።

አክባሪህ ኪዳናዊ ወንድምህና ክህነታዊ ባልደረባህ፡
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ።